

# የ2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫን በተመለከተ የአይአርአይ-ኤንዲአይ (IRI-NDI) የምርጫ ታዛቢ ልዑካን ቡድን የቅድመ ምርጫ ግምገማ ሪፖርት

ግንቦት 05 ቀን 2013 ዓ.ም.

Election Mission
IRI
NDI
Ethiopia 2021

የ2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫን በተመለከተ የአይአርአይ-ኤንዲአይ (IRI-NDI) የምርጫ ታዛቢ ልዑካን ቡድን የቅድመ ምርጫ ግምገማ ሪፖርት

የቅጂ መብቱ የተጠበቀ ነው © 2013 ዓ.ም. ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI)

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የዚህ ሥራ ክፍሎች ከንግድ ውጭ ለሆኑ ዓላማዎች ሊባዙ እና/ወይም ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የሥራው ምንጮች መሆናቸው ሊገለጽ እና የትርጉሙ ቅጂ ሊላክላቸው ይገባል። ቅጂዎቹን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡-

በተለይ ለውጭ ጉዳይ መምሪያ
ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት
1225 Eye Street NW, Suite 800
Washington, DC 20005
info@iri.org

በተለይ ለግንኙነት መምሪያ
ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት
455 Massachusetts Ave NW, 8th Floor
Washington, DC 20001
http://www.ndi.org/contact

# መግቢያ

ኢትዮጵያ የፊታችን ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም ለማድረግ ያቀደችው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ እየተቃረበ ሲሆን፣ ይህ ሀገር አቀፍ ምርጫ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከታየው ዘርፈ ብዙ የለውጥ እንቅስቃሴ እንዲሁም ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ማግስት የሚደረግ ከመሆኑም ባሻገር ሀገሪቷ በሲቪል አስተዳደር ስር የምታደርገው ስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ነው። የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀረበውን ግብዣ፤ የተሰጣቸውን የምርጫ ታዛቢነት ዕውቅና እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሕጎች እና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (አይአርይ) እና ናሽናል ዲሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት (ኤንዲአይ) በጋራ በመሆን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮ (IEAME) በማከናወን ላይ ያሉ ሲሆን፣ ግምገማው የሚከናወነውም በዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢነት ስልት መሰረት ነው።

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልእኮ (IEAME) ዘዴ፡- ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልእኮ ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢነት ስልትን በመጠቀም የተከናወነ ነው። አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ምርጫ ምዘና ተልእኮ ዓላማው ለኢትዮጵያ ዜጎች እና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ገለልተኛ እና ትክክለኛ የምርጫ ምህዳር ግምገማ ውጤቶችን ማቅረብ እንዲሁም ዓለም አቀፍ እና አካባቢያዊ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ደረጃዎችን እና የኢትዮጵያን ሕጎች መሰረት ያደረገ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው ወረርሽኝ ባስከተላቸው ማነቆዎች ምክንያት ተልዕኮው በዋነኝነት እየተከናወነ ያለው በዓለም አቀፍ የዲሞክራሲያዊ ምርጫ ታዛቢነት መርሆዎች ሕግ መሰረት ስልታዊ የርቀት ክንውን ዘዴን በመጠቀም ሲሆን፣ ይህም የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መርሆዎችን ጨምሮ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የምርጫ ሕጎች መሰረት ባደረገ መንገድ ገለልተኛ እና ከአድልኦ የጸዳ ግምገማ በማከናወን ነው። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምላሽ ለመስጠት ሲባል ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልእኮው ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የህዝብ ጤና መመሪያዎችን ይከተላል። ይህ ኤንዲአይ/አይአርአይ በጋራ የሚያከናውኑት ተልእኮ የገንዘብ ድጋፉን የሚያገኘው ከአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩኤስኤአይዲ) ነው።

የዚህ የምርጫ ግምገማ ስልት አንደኛው ወሳኝ አካል ኤንዲአይ/አይአርአይ ከሚያዝያ 1 እስከ 18 ያከናወኑት የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮ (VPEAD) ሲሆን፣ ቀጥሎ የተመለከቱትን የቅድመ ምርጫ ከባቢ ሁኔታ ግምገማ ትንተና በማቅረብ ኢትዮጵያ በግንቦት ወር ለምታደርገው ሀገር አቀፍ ምርጫ እንድትዘጋጅ ምክረ ሀሳብ አቅርበዋል። ይህ ትንታኔ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ አመራሮችን፣ የመንግስት ኤጀንሲዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ መገናኛ ብዙሀንን፣ የምርጫ ታዛቢዎች የሆኑ ዜጎችን እና የዲፕሎማሲውን ማህበረሰብ ጨምሮ ከበርካታ የምርጫ እና የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ጋር በበይነ መረብ የተደረጉ ቃለ መጠይቆችን እንዲሁም የተቋማቱን ባለሞያዎች እና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሏቸውን ግንኙነቶች መሠረት በማድረግ በወቅቱ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው።

የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮው (VPEAD) የኤንዲአይ ቦርድ አባል እና የቀድሞ የዩናይትድ እስቴትስ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ጸሀፊ በሆኑት በአምባሳደር ጆኒ ካርሰን፤ የአይአርአይ የቦርድ አባል እና የቀድሞ የዩናይትድ እስቴትስ የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ጸሀፊ በሆኑት በተከበሩ ኮንስታንስ ቤሪ ኒውማን፤ እና የቀድሞ የኬኒያ ገልተኛ የምርጫ ቦርድ እና የድንበር ኮሚሽን ሊቀመንበር በሆኑት በተከበሩ አህመድ ኢሳክ ሀሰን የተመራ ነበር። የልዑካን ቡድኑ የሚከተሉትን የምርጫ እና የአካባቢ ባለሞያዎች ያካተተ ነው፡- የኤንዲአይ ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑትን ሻሪ ብሪያንን፤ የአይአርአይ አፍሪካ ዲቪዥን ዳይሬክተር የሆኑንት ግሪጎሪ ኪርንስን፤ የኤንዲአይ ምክትል የደቡብ እና ምስራቃዊ አፍሪካ ሪጅናል ዳይሬክተር የሆኑትን ጀሚማ ናቪስ ባርሎውን፤ እንዲሁም የአይአርአይ ከፍተኛ የአፍሪካ አማካሪ የሆኑትን ምቼምባ ፊዞ ዲዞሌሌን። በተጨማሪም የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮው (VPEAD) የዓለም አቀፉ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮ (IEAME) ሚሽን ዳይሬክተር በሆኑት በስቴፈኒ ሞንዶን እና ምክትል የሚሽን ዳይሬክተር በሆኑት በስቴፈን ዝዌድ፤ የሀገር ውስጥ ረዳት ኖሯቸው ከርቀት የሚሠሩ የረጅም ጊዜ የዘርፍ ትንተና ባለሞያዎች (LTAs)፤ በረጅም ጊዜ የዘርፍ ትንተና አስተባባሪ እና በአይአርአይ እንዲሁም በኤንዲአይ በሚገኙ በጉዳዩ ላይ የሚሰሩ የዋና መሥሪያ ቤት ቡድኖች የተደገፈ ነበር። በአዲስ አበባ በምርጫ ሰሞን አነስተኛ የቴክኒክ ቡድን ተዋቅሮ ወደ ስራ የሚገባ ሲሆን፣ ምርጫውን ተከትሎ በዓለም አቀፉ የኢትዮጵያ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮ (IEAME) ለሚዘጋጀው የመጨረሻ ሪፖርት ሁሉም አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽ ያደርጋሉ።

ሁሉም የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮው ምክክሮች ከፓርቲ ውግንና ሙሉ በሙሉ ነጻ በሆነ መንገድ የተከናወኑ ሲሆን፣ በምርጫ ሂደቱ ላይ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት አልነበረም። የዓለም አቀፍ ትብብር መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በአይአርአይ/ኤንዲአይ የቀረቡት የቅድመ ምርጫ ትንታኔዎች ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለማጠናከር እና ውጤታማ የምርጫ አሰራሮችን እውን ለማድረግ፣ የዲሞክራሲ ተቋማትን ለመገንባት፣ አስቻይ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም የዜጎችን ተሳትፎ ለማጎልበት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ተጠያቂነት ለማስፈን ለምታደርጋቸው ጥረቶች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንደሚሆኑ ይታመናል። ተልዕኮው የመረጃ ልውውጥ ላደረጉለት እና አመለካከቶቻቸውን ላጋሩት አካላት በሙሉ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል። ምርጫ የህዝቦች ሉአላዊነት ማሳያ እንደመሆኑ መጠን የምርጫውን ሂደት ባህሪያት የመገምገም እና ለወደፊቱ ዴሞክራሲን የማጎልበት ዕድሎችን በአግባቡ የመጠቀም መብት ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑ ግልጽ ነው። አይአርአይ እና ኤንዲአይ አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን እስከ ፍጻሜው ድረስ መገምገማቸውን ይቀጥላሉ።

# የማጠቃለያ ግኝቶች እና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ምክረ ሃሳቦች

ግንቦት 28 ይካሄዳል ተብሎ ቀን የተቆረጠለት የኢትዮጵያ የ2013 ምርጫ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረጉ የህግ ማሻሻያዎችን መሠረት በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ሁሉን አቀፍ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል መልካም ዕድል ሊፈጥር ይችላል የሚል ተስፋ አለ። ሆኖም በስፋት የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮችን እና የብሔር ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከሚከናወኑ የእጩዎች እና የመራጮች ምዝገባ ሥነ-ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ መዘግየቶችን፣ አንዳንድ የክልል መንግስታት ደካማ የሆነ ትብብር ማሳየታቸውን፣ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ያላቸው በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ሂደቱ ራሳቸውን ማግለላቸውን እና እናገላለን የሚል ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ እንዲሁም ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን የህዝብ ጤና ቀውስ ጨምሮ አዳጋች የሆኑ የተለያዩ ጉልህ ችግሮች መኖራቸው መራጮች እና ፓርቲዎች በሂደቱ ውስጥ ለመሳተፍ ባላቸው አቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር እና በዚህም ተዓማኒነት ያለው ምርጫ የመከናወኑን ዕድል እንዳያጠበው ያሰጋል። በመሆኑም ከምርጫ ቀን አስቀድሞ በሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚከወኑ ሁነኛ እና የተቀናጁ ጥረቶች ትርጉም ያለው ምርጫ ለማካሄድ እና ከምርጫው ባሻገር ለብሄራዊ እርቅና ለዴሞክራሲያዊ እድገት መሰረት ለመጣል አስፈላጊ ግብአቶች ናቸው።

ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ የተተገበሩት የህግ እና የፖለቲካ ማሻሻያዎች ለዜጎች፣ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለመገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ነፃነቶችን ያጎናፀፉ በመሆናቸው መጠነ ሰፊ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ለውጦችን አስከትለዋል። ከምርጫ እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ግንኙነት ባላቸው ሕጎች ላይ የተደረጉ ለውጦች ቀደም ሲል በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ የነበሩ በርካታ ገዳቢ ይዘቶችን አስወግደዋል። የወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የቦርዱ ሰብሳቢ ሆኖ መሾም ቀደም ሲል የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ እና በከፍተኛ ደረጃ የተከበሩ ዳኛ የነበሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የፖለቲካው ማህበረሰብ በአጠቃላይ ለምርጫ ቦርድ የሚሰጠው አክብሮት እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በተጨማሪም ምርጫ ቦርድ በሚተዳደርባቸው ሕጎች ላይ የተደረጉ ለውጦች የቦርዱን ድርጅታዊ ነፃነት አሻሽለዋል። ምርጫ ቦርድ በቦርዱ ሰብሳቢ ወ/ሪት ብርቱካን መሪነት ተዓማኒ ምርጫዎችን የማካሄድ አቅሙን ለማጎልበት እና የህዝቡን እምነት ለማትረፍ ረዥም ሂደቱን ጀምሯል። ከምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋ በተጨማሪ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቷ እና የኢፌዲሪ ፕሬዝዳንቷ ሴት መሆን ሴቶች በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ሊጫወቱት የሚችለውን ወሳኝ ሚና ያሳያል። በተጨማሪም ለረጅም ጊዜ ተሳትፏቸው ተገድቦ የነበረው የሲቪል ማኅበረሰብ አስተዋጽኦ በስነ ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት እንዲሁም በምርጫ ሂደት ገለልተኛ ታዛቢ መሆን እንዲችሉ እንደገና ዕድል በመፈጠሩ ሲቪል ማህበራቱ በምርጫ ሂደቱ ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መርምሮ መፍታት የሚቻልባቸውን ምክረ ሃሳቦች ማቅረብ ጀምሯል። እነዚህ ተሞክሮዎች ከዚህ ቀደም የነበሩት ሁኔታዎች መቀየራቸውን የሚያሳዩ በመሆናቸው ወሳኝ ናቸው እንዲሁም የበለጠ ሊበረታቱ ይገባል።

ከዚህ ጎን ለጎን በምርጫ ምህዳሩ ውስጥ ያሉ ከባድ እና አሳሳቢ ተግዳሮቶች አሉ። በስፋት ተቃውሞ የገጠማቸው በ1997፣ በ2002 እና በ2007 የተካሄዱት ምርጫዎች እና ከዚያ ጋር ተያይዞ የነበረው የፖለቲካ ጭቆና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችንም ጭምር አቅም ያሰናከለ ሲሆን ይህም እነዚህ አካላት በአሁኑ ወቅት በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ላይ የራሱን ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው። ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ ከቆዩ የብሔር ውጥረቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው በርካታ የጸጥታ ቀውሶች ያጋጠሟት ሲሆን ይህም በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ በርካታ አካባቢዎች ያለመረጋጋትን ወይም ግልጽ ግጭትን አስከትሏል። የፀጥታ ሁኔታው ህዝቡ በነፃነት እና በንቃት በምርጫ ለመሳተፍ ያለውን ብቃት የሚያዳክም በመሆኑ አንዳንድ ወገኖች ከሂደቱ ራሳቸውን እንዲያገሉ ምክንያት ሆኗል። ግልፅ ግጭት በመኖሩ የተነሳ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ምርጫ አይካሄድም። በርካታ ታዋቂ የኦሮሞ የፖለቲካ መሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር መዋላቸው በኢትዮጵያ ትልቁን የሕዝብ ቁጥር በሚይዘው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ሂደቱ ራሳቸውን በማግለል ተቃውሟቸውን እንዲገልጹ ምክንያት ሆኗል። የፀጥታና የደህንነት አስተማማኝ አለመሆን የሴቶችን፣ የካል ጉዳተኞችን እና የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ ዜጎችን የምርጫ ተሳትፎ በተለየ መልኩ ይጎዳል። የሚዲያ ነፃነት ላይ የላቀ መሻሻል የታየ ቢሆንም መደበኛ መገናኛ ብዙሃን አሁኑንም በአመዛኙ በመንግስት ደጋፊዎች ድምፆች የበላይነት የተያዙ ናቸው። በተጨማሪም በሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ውስጥ ባሉ ግለሰቦች የተሳሳቱ መረጃዎችን ማሰራጨት በስፋት መስተዋሉ የመራጮችን ትክክለኛ መረጃ የማግኘት ዕድል ያስተጓጉላል። የጥላቻ ንግግሮች መበራከትም የምርጫውን ድባብ አደብዝዞታል። ሴቶች ወደ ከፍተኛ የአመራር ሃላፊነት ቦታዎች መምጣታቸው ሳይጠቀስ የማይታለፍ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ሴቶች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በምርጫ ሂደት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ውስን ነው። በስፋት እየተሰራጨ ያለው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የማህበረሰቡን የጤና ሁኔታ አስጠብቆ ታማኝነት ያለው ምርጫን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማድረግ ተጨማሪ ፈተና ሆኖ ተጋርጧል። እነዚህ ጉዳዮች የምርጫውን ታማኝነት ስጋት ላይ የሚጥሉ በመሆናቸው በእጩዎች መረጣ እና በመራጮች ምዝገባ ሂደቶች ላይ ገና ከአሁኑ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድረዋል።

ሆኖም ግን ይህ ምርጫ አዎንታዊ እርምጃ ሊሆን እና ወደ ፊት ይበልጥ ተአማኒነት ያላቸው ሂደቶች እንዲኖሩ መሠረት ሆኖ ሊያገለግል የሚችልበት መልካም ዕድል አለ። የልዑካን ቡድኑ ምርጫው ይፋ በተደረገው መሰረት መከናወኑን የሚደግፉ እንዲሁም የሚቃወሙ አካላትን ሃሳብ አድምጧል። ምርጫው የሚደረግበት ጊዜ መቼም ቢሆን የምርጫውን ድባብ ለማሻሻል የተቀናጁ ጥረቶች ያስፈልጋሉ። እስከ ምርጫ ቀን ድረስ ባለው ውስን ጊዜ ውስጥም ቢሆን የ2013 የኢትዮጵያ ምርጫ እንዲሁም ለወደፊቱ የሚደረጉ ምርጫዎች ሀገሪቱን ወደፊት የሚያራምዱ እንዲሆኑ ለማገዝ ኢትዮጵያውያን ሊወስዷቸው እና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሊደግፋቸው የሚችሉ ወሳኝ እርምጃዎች አሉ። የዴሞክራሲ መስፋፋትን ለማጎልበት ኢትዮጵያውያን ለሚያደረጓቸው ጥረቶች አዎንታዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ተስፋ በማድረግ፣ ከኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት እና ከናሽናል ዲሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት የተጣመረው የልዑካን ቡድን የ2013ቱን ምርጫ ሁሉን ያካተተ፣ ግልፅ እና ተጠያቂነትን የተላበሰ ለማድረግ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ቅድሚያ ሰጥተው ሊተገብሯቸው የሚገቡ 12 ምክረ ሃሳቦችን አቅርቧል።

# ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ምክረ ሃሳቦች

## የምርጫን ነባራዊ ሁኔታ በተመለከተ

**የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ ኃይሎች ለመራጮች እና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ደህንነቱ የተጠበቀ አከባቢን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።** እየተስፋፋ የመጣው አስተማማኝ ያልሆነ የፀጥታ ሁኔታ ኢትዮጵያውያን በምርጫ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የመቀነስ አዝማሚያ እያሳየ ሲሆን በተጨማሪም በምርጫ ቀን የሚደረገውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እንዳያስተጓጉል ያሰጋል። የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ አካላት ከምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር መራጮችን፣ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ እጩዎችን፣ ደጋፊዎቻቸውን፣ መራጮች ትምህርት የሚሰጡ ተቋማትን እና ታዛቢዎችን ጨምሮ በመላ አገሪቱ በምርጫው ሂደት ለሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት በሙሉ ተሳትፎአቸው ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ እንዲሆን የፀጥታ ቡድን የማዋቀር እና የማሰማራት ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው። የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ ኃይሎች ያለምንም አድሎአዊነት ሥራቸውን ለማከናወን እና በምርጫው አካሄድ ውስጥ ጣልቃ ላለመግባት በይፋ በመወሰን ቁርጠኝነታቸውን ማሳየት አለባቸው።

**ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአመፅ፣ ከማስፈራራት እና ከጥላቻ ንግግሮች እራሳቸውን በመቆጠብ በይፋ ለሰላም ጥሪ ማድረግ አለባቸው።** የቱንም ያህል በኢትዮጵያ የፖለቲካ በማህበርሰብ ውስጥ ጥልቀት ያላቸው ውዝግቦች ቢኖሩም፣ ሁሉም ዜጎች ያለምንም የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ደህንነታቸው ተጠብቆ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ ዕድል ሊኖራቸው ይገባል። በምርጫ የሚሳተፉም ሆነ ከምርጫ ሂደቱ እራሳቸውን ያገለሉ ሁሉም ፓርቲዎች በአደባባይ ሁከትን በማውገዝ አገራዊ የሰላም ጥሪ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ውጥረትን ለመቀነስ በተጠናከረ ሁኔታ ተከታታይ ውይይት ማካሄድ ይኖርባቸዋል።** ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሃይል የቀላቀሉ ግጭቶች፣ ማስፈራሪያዎች እና የጥላቻ ንግግሮች ሥጋቶችን ለማስቀረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ የውይይት መድረኮችን በየጊዜው ሊያመቻች ይገባል። ፓርቲዎች በምርጫ ሥነ ምግባር ደንቦች ለመገዛት ቁርጠኝነታቸውን ሊሲያዩ የሚገባ ሲሆን ደንቡን የሚቃረኑ አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ተጠያቂ ማድረግ አለባቸው።

**ኢትዮጵያውያን ደህንነታቸው ተጠብቆ በምርጫ ሂደቱ እንዲሳተፉ የኮቪድ-19 የመከላከያ እርምጃዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ መከተል ያስፈልጋል።** የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም የቀጠለ ሲሆን፣ እስከ ምርጫው ባለው ጊዜ የበለጠ ሊባባስ ይችላል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመራጮች ምዝገባ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የደኅንነት ፕሮቶኮሎችን ቢያዘጋጁም፣ የመራጮች በተለይም በገጠር አካባቢዎች እነዚህን መመርያዎች በስፋት የማክበር ጉዳይ ላይ ያለው መረጃ ግልጽ/አስተማማኝ አይደለም። ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅን የተመለከቱ ግልጽ መመሪያዎች በፖለቲካ ፓርቲዎች በሚደረጉ ቅስቀሳዎች ወቅት እና በምርጫ ጣቢያዎች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፤ ምርጫው በሚከናወንባቸው ስፍራዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ ግዴታ መሆን አለበት፤ እንዲሁም በሚያስፈልገው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሳሙና/የሳኒታይዘር የምርጫ ጣቢያዎች ላይ መሰራጨት አለባቸው።

**የፌዴራል እና የክልል ባለሥልጣናት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሴቶችን የምርጫ ተሳትፎ ለማሳደግ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።** ሴቶች ላይ ሊደርስ የሚችል ፆታዊ ጥቃት፣ የፀጥታ መደፍረስ፣ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በቤተሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጫናዎች መኖራቸው፤ እንዲሁም ነባር ማህበራዊ እና ባህላዊ አመለካከቶች ሴቶች በምርጫ ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ እንቅፋት ይፈጥራሉ። የመንግሥትና የምርጫ ተዋንያን እዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ተገቢውን እርምጃ ለመሰድ የሚያስችሉ ዝግጅቶችን በሚደርጉበት ወቅት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም በተለይ ደግሞ የሥርዓተ-ፆታ ባለሙያዎችን ማካተት አለባቸው። ሴቶች ለድምፅ ሰጪነት እንዲመዘገቡ፣ ድምጽ እንዲሰጡ፣ የምርጫ አስፈፃሚ እንዲሆኑ፣ በእጩነት እንዲሳተፉ፣ የምርጫ ታዛቢዎች እንዲሆኑ እና በአጠቃላይ በምርጫ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማበረታታት ጠንካራ እርምጃዎችን መውሰድ እና በይፋ መግለጫዎችን ማውጣት ይገባል።

## የምርጫ ዝግጅቶች

**ለምርጫው የሚደረጉ ዝግጅቶችን ለማጠናከር የፌዴራል እና የክልል መንግስታት ተቀናጅተው መሥራት እና ለምርጫ ቦርድ ሁሉንም አስፈላጊ ድጋፎች እና ሀብቶች ማቅረብ አለባቸው።** የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን ለማካሄድ የሚያስችል በቂ ድጋፍና ግብዓት ላያገኝ ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት አሁንም አለ። በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እና በአገራዊ የትብብር መንፈስ የፌዴራልና የክልል ባለሥልጣን አካላት የምርጫውን ሂደት በሁሉም መልኩ ከማደራጀት እና ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ የምርጫ ቦርድን እንዲሁም በክልል እና በምርጫ ክልል ደረጃ ያሉ ጽ/ቤቶቹን ለማገዝ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በሁሉም ሁኔታዎች የመንግስት ባለሥልጣናት በምርጫ ሂደት ሰፊ የመራጮችን እምነት ለማግኘት እንዲቻል በማያዳላ መልኩ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

**በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ዜጎችን ጨምሮ ሁሉም ለድምፅ መስጠት ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለመመዝገብ እና ድምጽ ለመስጠት ትርጉም ያለው ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ መደረግ አለበት።** ምርጫ ቦርድ ለመራጮች ምዝገባ ሁሉንም የምርጫ ጣቢያዎች ለመክፈት ከፍተኛ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የምዝገባ እና ድምጽ የመስጠት ሂደት ለማስፈፀም ተልእኮ ተሰጥቶታል። ሆኖም በክልል መንግስታት በኩል ያለው ውስን ትብብር የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ለማቋቋም እና እነኚህ ዜጎች እንዲመዘገቡ ለማስቻል ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያለውን እቅድ ተፈፃሚ እንዳያደርግ አግዶታል። የፌዴራል እንዲሁም የክልል መንግስታት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ጨምሮ ለመምረጥ ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በምርጫው ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ተደራሽነት መፍጠር አለባቸው።

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመራጮች ምዝገባ ዙሪያ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ መስጠት አለበት።** የመራጮች ምዝገባ መጠን በአጭር ቀናት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ምክንያት የብሔራዊ እና የክልል ምዝገባ ቁጥሮች ላይ በከፊል ጥርጣሬ ተፈጥሯል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የበለጠ ለማስረዳት ዝርዝር የምዝገባ መረጃዎችን በመስጠት ከህጉ መስፈርቶች ባሻገር እንዲሄድ እና የህዝብ አመኔታን እንዲያሳድግ ይበረታታል። የሚሰጡት መረጃዎች በቀን፣ በወረዳ፣ በጾታ እና ዕድሜ የተከፋፈሉ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም በተደራሽ የምርጫ መረጃ (openelectiondata.net) መርሆዎች መሠረት የመራጮች ዝርዝር ቅጅዎችን በኤሌክትሮኒክ የመልእክት ማተላለፊያ ዘዴ መልክ ማቅረብ ይችላል።

**በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት አማካኝነት ከስነ ዜጋ እና ከመራጮች ትምህርት ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ሥራዎች የፀጥታ ችግር ያለባቸው፣ የመረጃ ተደራሽነት የሌላቸው እና የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን የበለጠ ባካተተ መልኩ ተጠናክረው ሊሰሩ ይገባል።** ሁሉም ኢትዮጵያዊ በምርጫው የመሳተፍ ዕድል እንዲኖረው ለማድረግ ተጨማሪ የስነ ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ጥረቶች ያስፈልጋሉ። የመራጮች ምዝገባ በዘገየባቸው እና የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የስነ ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ለማህበረሰቡ በአስቸኳይ እንዲዳረስ ያስፈልጋል። በስነ ዜጋ እና በመራጮች ትምህርት አሰጣጡ ሂደትም ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን እና ሌሎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማካተት ተጨማሪ ጥረቶች መደረግ አለባቸው።

የመገናኛ ብዙሃን ሚዛናዊ የምርጫ ሽፋን ለመስጠት እና መረጃ የማጣራት እና የተዛቡ/የሐሰት መረጃዎችን ለመዋጋት በሚያስችል መልኩ የእውነታ ማጣሪያ ስርዓቶችን ለማጠናከር የተቀናጀ ጥረት ማድረግ አለባቸው። በምርጫው ላለመሳተፍ የወሰኑትን ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግስት ቁጥጥር ስር ባሉ የህዝብ መገናኛ ብዙሃን ፍትሃዊ ሽፋን ማግኘት አለባቸው። የግል መገናኛ ብዙሃንም በተመሳሳይ መልኩ የፖለቲካ አመለካከቶች ብዝሃነትን ጠብቀው መረጃዎችን ለማቅረብ መጣር አለባቸው። የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች እና ጋዜጠኞች የመረጃ ምንጮችን ለማጣራት እና እውነታውን የመፈተሽ ስልቶችን ለማጠናከር ጥረታቸውን በእጥፍ ማሳደግ አለባቸው። ይህም ሂደት ዜጎች የምርጫውን ሂደት እና እጩዎችን በተመለከተ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኙ በማኅበራዊ እና በመደበኛ የመገናኛ ብዙሃን ሚሰራጩ የውሸት መረጃዎችን ለማጋለጥ ያግዛቸዋል።

# የምርጫ ቀን እና የድህረ ምርጫ ማግስት

የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫውን ለመታዘብ እና ግኝታቸውን ለህዝብ ለማጋራት ያልተገደበ ነፃነት ይፈልጋሉ። ለምርጫ ታዛቢዎች የእውቅና አሰጣጥ አሰራሮች እና መመሪያዎች አግባብ ባልሆነ መልኩ ቢሮክራሲያዊ እና ገዳቢ ናቸው። ገለልተኛ የሆኑ የምርጫ ታዛቢዎች በተለይም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ የተወጣጡ የዜጎች ታዛቢዎች የሂደቱን ታአማኒነት በመጠበቅ እና ግኝቶቻቸውን በይፋ በማካፈል ዜጎች በምርጫዎች ላይ እምነት እንዲኖራቸው ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የእውቅና አሰጣጥ አሰራሮችን ማቀላጠፍና ማፋጠን እንዲሁም ታዛቢዎች ግኝታቸውን በወቅቱ በይፋ እንዲያካፍሉ መፍቀድ አለበት።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የውጤት ማቅረቢያ እና ማሳወቅያ ሂደት ሁሉን አቀፍ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ያለፉት የምርጫ ውጤቶች ላይ በሰፊው ይነሱ የነበሩ አለመተማመኖችን በዚህኛው ምርጫ ውቅት ለማስቀረት እንዲቻል ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የተገኙ የቆጠራ ውጤቶችን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ በፍጥነት እንዲመዘገቡ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። የህዝብ አመኔታን ለማሳደግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የውጤት ማሳወቅ ሂደቱ በምን መልኩ እንደሚከናወን ለህዝብ እና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ማስረዳት አለበት። ሁሉንም ስርዓቶች እና የአሰራር ሂደቶች ከምርጫው ቀን በፊት በደንብ መፈተሽ እና ግኝቶቹን ለባለድርሻ አካላት ማጋራት ተገቢ ነው። በውጤቶቹ ላይ ህዝባዊ አመኔታን ለማሳደግ የሁሉም የምርጫ ጣቢያ ውጤቶች በኤሌክትሮኒክ መንገድ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በይነ-መረብ (ኢንተርኔት) ገፅ ላይ በወቅቱ መታተም እና ለህዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው።

ከእነዚህ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ምክረ ሃሳቦች ባሻገር የሕግ ማዕቀፉን ለማሳደግ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የበለጠ ለማጠናከር ከምርጫ በኋላ ጉልህ እና የረጅም ጊዜ ጥረቶች ያስፈልጋሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወካይነት ማሳደግ፣ ቀልጣፋ የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎን ማበረታታት፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ዜጎች እና ሌሎች የተገዱ የማህበረሰብ ክፍሎች የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ እና ሚዛናዊና ትክክለኛ የሆኑ መደበኛ እና ማህበራዊ ሚዲያዎችን የማቅረብ ሂደት ላይ የበለጠ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ተአማኒነት ያላቸው ምርጫዎች እና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን የሚሆኑት የአገሪቱ የፀጥታ ችግሮች ሲፈቱ ነው። ከዚህ አንፃር ታሪካዊ ቅሬታዎችን ትርጉም ባለው መልኩ ለመፍታት ሁሉን አቀፍ አካሄድ መከተል፣ እናም የሀገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ስር የሰደዱ የህብረተሰብ ክፍፍሎችን እና የጎሳ ውጥረቶችን ለመፈወስ ፍትህ እና ብሄራዊ እርቅ እንዲኖር አስፈላጊ ነው።

# የፖለቲካው አውድ

የፊታችን ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. የሚደረገው ምርጫ ሀገሪቱ ወደ ሲቪል አመራር ከተመለሰች ወዲህ ስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም ሀገሪቷ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያደረገቻቸው ምርጫዎች ጥልቅ ችግር የነበረባቸው ተደርገው የታዩ ነበሩ እንዲሁም ተአማኒነት ያለው ምርጫ ከማድረግ እና የምርጫ ተቋማትን ከመገንባት አንጻር ያላት ተሞክሮ ውስን ነው። በ2010 ዓ.ም. ሚያዝያ ወር ላይ አብይ አህመድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ከመጡበት ጊዜ አንስቶ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋትን፣ ሰፊ ነጻነት መፍቀድን እና ተአማኒነት ያለው ምርጫ ከማድረግ አንጻር አውንታዊ አመለካከት መፍጠርን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ የለውጥ ስራዎች ተሰርተዋል። በርካታ ሴቶችን ጨምሮ በህዝብ ዘንድ አክብሮትን ያተረፉ ታዋቂ ግለሰቦች በተቋም አስተዳዳሪነት ወደ ስልጣን መምጣታቸው በህዝብ ዘንድ ያለውን መተማመን ይበልጥ አጎልብቶታል። ሆኖም ለበርካታ ዘመናት የተዘራ እና ታፍኖ የቆየው በብሔሮች መካከል ያለው ውጥረት ወደ መድረክ ብቅ ብሏል። ስለሆነም ምርጫው የሚደረግበት አውድ በስፋት የጸጥታ ስጋት ያለበት፣ የፖለቲካ አፈና ተጋላጭነት ያልጠፋበት፣ ግልጽ ግጭቶች እና በክልሎች መካከል ውጥረት ያንዣበበበት እንደሚሆን ይገመታል። እነዚህ ሁኔታዎች ተአማኒነት ያለው ምርጫ እንዳይካሄድ ጋሬጣ የሚፈጥሩ ሲሆን የዜጎችን እንዲሁም በተለይም ደግሞ የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምርጫ ተሳትፎ የሚገድቡ እንቅፋቶችን ሊያባብሱ ይችላሉ።

ኢትዮጵያ ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት በብሔር እና በክልል በተደራጀ አንድ አውራ ፓርቲ አመራር ስር የቆየች ቢሆንም በ2011 ዓ.ም ኢህአዴግ ከፈረሰ ወዲህ ሀገሪቷ የምታደርገው የመጀመሪያው ምርጫ ተቃርቧል። ኢህአዴግ አራት ፓርቲዎችን ያቀፈ ግንባር የነበረ ሲሆን፣ እነሱም የትግራይ ህዝቦች ነጻነት ግንባር (ትህነግ)፣ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን፣ በኋላ ላይ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የሆነው)፣ የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) እና የደቡብ ክልል ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደህዴን) ናቸው። ኢትዮጵያ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር በነበረችበት ወቅት የብሔር ግጭቶች፣ ሙስና እና የመሰረታዊ ነጻነቶች ያለመከበር የፖለቲካ አውዱ መገለጫዎቹ ነበሩ። እነዚህ ሁኔታዎች የፖለቲካ ተሳትፎን እና የፖለቲካ ውድድርን እንዲሁም የሚዲያ እና የሲቪል ማህበራት ተሳትፎን በእጅጉ ያቀጨጩ ነበሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ (ዶ/ር) በሚያዚያ ወር 2011 ዓ.ም ወደ ስልጣን ከመጡበት ጊዜ አንስቶ መንግስታቸው ዜጎች መሰረታዊ የሆነ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመደራጀት እና የመሰባሰብ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ የፖለቲካ እና ሲቪል ምህዳሩን የማስፋት ዓላማ ያላቸው በርካታ አዎንታዊ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ከማድረጉም ባሻገር በፌዴራል መንግስት እና በክልል መስተዳድሮች መካከል ያለውን ግንኙነት በአዲስ መልኩ ቅርጽ የማስያዝ ዓላማ ያላቸው ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። በርካታ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማህበራዊ አገልግሎት በማቅረብ ብቻ ተገድበው መቆየታቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ዕድገት ውስጥ ባለ ድርሻ በመሆን በምርጫው ሂደት እንዲሳተፉ ፈቃድ አግኝተዋል። ለዚሁ አላማ ሲባል በርካታ የሰብአዊ መብት አንቂዎች (አክቲቪስቶች) የመንግስት ተቋማት አመራር ቦታዎች ላይ ለመሾም የቻሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተጠቃሽ ናቸው።

የሪፎርም አጀንዳውን አስከትሎ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ከእስር የተፈቱበት ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም በርካታ ከሀገር ተሰደው የነበሩ አክቲቪስቶች እና ተቃዋሚዎች ራሳቸውን በማደራጀት ለነሀሴ 2012 ዓ.ም. ታቅዶ የነበረው እና በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ወደ ግንቦት 2013 ዓ.ም የተዛወረው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። የፖለቲካ እስረኞች መለቀቃቸው በርካታ የክልል እና ሀገር አቀፍ አዳዲስ ፓርቲዎች እንዲመሰረቱ ያስቻለ ከመሆኑም ባሻገር ውድድር የሰፈነበት ምርጫ ለማድረግ እና ለወደፊቱም በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማስፈን አዲስ ተስፋን ፈጥሯል።

ሆኖም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመሩት ማሻሻያዎች በተሟላ ደረጃ አለመተግበራቸውን አስመልክቶ ስሞታዎች መደመጥ የጀመሩ ሲሆን፤ በተለይም ትግበራው ከፌዴራል እስከ ክልሎች እና አካባቢ ደረጃዎች ድረስ ወርዶ እውን አልሆነም የሚሉ ቅሬታዎች አሉ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሁንም ደካማ ናቸው፣ ዳግም እራሳቸውን ለማደራጀት ተግዳሮቶች ገጥመዋቸዋል እንዲሁም ያላቸው የገንዘብ እና የሰው ሀብት ውስን ነው። በስልጣን ላይ ጠንካራ ፓርቲ መኖሩ እንዲሁም አዳዲስ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መቋቋማቸው የምርጫ መጫወቻ ሜዳውን ያልተመጣጠነ አድርጎታል። በስልጣን ላይ የነበረውን የፓርቲዎች ጥምረት ዳግም ለማዋቀር የተደረገው ጥረት በፖለቲካ ሊሂቃን በተለይም በትህነግ አባላት ዘንድ ሰፊ ተቃውሞ ያጋጠመው ሲሆን፣ ፓርቲው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ገኖ እና የኢህአዴግን አመራር ተቆጣጥሮ መቆየቱ ይታወሳል። ተግባራዊ የተደረጉት ለውጦች አንዲት-ኢትዮጵያ በሚለው ብሔራዊ ራዕይ በሚመራው ለውጥ አቀንቃኞች እና ብሔርን መሰረት ባደረገው የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ሥርዓት ደጋፊዎች መካከል ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። የኢህአዴግ መልሶ መዋቀር በሂደት ብልጽግና ፓርቲ የተባለ አዲስ ፓርቲ ወደመፍጠር ያመራ ቢሆንም ትህነግ ይህን ፓርቲ ለመቀላቀል ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም የትህነግ አመራር አካላት የምርጫውን ላልተወሰነ ጊዜ መራዘም በጽኑ መቃወማቸው ይታወሳል። ይህን ተከትሎም የትግራይ ክልል ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍሎች ተነጥሎ ለብቻው በጳጉሜ ወር 2012 ዓ.ም ክልላዊ ምርጫ ያደረገ ሲሆን ይህም ፖለቲካዊ አለመግባባቱን አባብሶታል፤ በተጨማሪም በክልል ደረጃ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለመታወጁ መንስኤ ሆኗል። ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የፌዴራሉ መንግስት ሰራዊቱን ወደ ትግራይ ክልል በማስገባት «ሕግ እና ስርዓት የማስከበር ወታደራዊ እንቅስቃሴ» ማወጁ ይታወሳል። ምንም እንኳን የፌዴራሉ መንግስት ወታደራዊ ተልእኮውን በጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቁን ይፋ ያደረገ ቢሆንም፣ በዚህ የተነሳ የተቀሰቀሰው ግጭት ረዘም ላሉ ወራት ቀጥሏል፣ እንዲሁም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የትግራይ ነዋሪዎች እንዲፈናቀሉ እና በቀጠናው ያለመረጋጋት ስጋት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ለኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት ድጋፍ ለማድረግ የኤርትራ ሰራዊት በጦርነቱ እንዲሳተፍ እንዲሁም በኢትዮጵያ እና በሱዳን ወታደሮች መካከል ለተፈጠረው ግጭት ምክንያቱ ተዳፍነው የቆዩ የድነበር ወሰን ውጥረቶች ናቸው። በዚህ ግጭት ምክንያት በትግራይ ምርጫ አይደረግም።

የብልጽግና ፓርቲ መመስረት በተለያዩ የኦሮሞ የማህበረሰብ ቡድኖች መካከል እንዲሁም በአማራ ክልል እና በትግራይ ክልል አመራሮች መካከል ውጥረትን ፈጥሯል። በኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ ውጥረቶች በተለያዩ መንገዶች የተከሰቱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከድንበር ጋር የተያያዙ የትጥቅ ግጭቶች፣ የተቃውሞ ሰልፎች፣ ምርጫ እንዳይደረግ ማደም እና የበርካታ ፓርቲዎች ከምርጫው ሂደት እራሳቸውን በማግለል ይገኙበታል። የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች በቁጥጥር ስር መዋል እንዲሁም መታሰራቸው እንዲሁም ምናልባትም በርካታ ደጋፊዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸው በኦሮሚያ መራጮችን ሊያርቅ ይችላል፣ ከዚህ አልፎም በአንዳንድ የምርጫ አካባቢዎች ውድድር የሰፈነበት ምርጫ እንዳይደረግ ተግዳሮት ሊፈጥር ይችላል። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ከሆነ በትግራይ ክልል የተፈጠረው ግጭት የውጭ ተዋንያን ከመሳተፋቸው ጋር ተደምሮ ሌሎች አካባቢያዊ የይገባኛል ጥያቄዎች እንዲነሱ ምክንያት ሊሆን እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ የባሰ አለመረጋጋትን ሊፈጥር ይችላል።

# የምርጫ ጸጥታ/ደህንነት እና ግጭት

ኢትዮጵያ በርካታ የጸጥታ ቀውሶች እያጋጠማት ያለ ሲሆን ዘላቂ የጸጥታ ስጋቶች የምርጫውን አስተዳደር ከማደናቀፋቸውም ባሻገር አጠቃላይ ተአማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ እንዳይከቱት ያሰጋል። ግጭት ቀስቃሾች የተለያዩ መልኮች ያሏቸው ሲሆን በኢትዮጵያ ያለውን ስር የሰደደ የብሄር ክፍፍል የሚያንጸባርቁ ናቸው። በግጭቶች እና የግጭት ስጋቶች በመኖራቸው ምክንያት የሚፈጠረው የጸጥታ ችግር በሴቶች፣ በአናሳ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በወጣቶች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና በሌሎች የተገለሉ ማህበረሰቦች የምርጫ ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተጽእኖን ያሳድራል።

በትግራይ ክልል ያለው ጦርነት፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል በተከታታይ የተከሰተቱት አለመረጋጋቶች፣ በምእራብ ኦሮሚያ እና በምስራቅ አማራ እየተባባሰ የመጣው ግጭት የደህንነት ሁኔታውን እያባባሱት ይገኛሉ። በተለይም ደግሞ በአፋር-ሶማሌ ድንበር አካባቢ በተከሰተው ግጭት ምክንያት እንዲሁም በአማራ አንዳንድ አካባቢዎች ባጋጠሙት ረብሻዎች የተነሳ በተለያዩ አካባቢዎች ኮማንድ ፖስት እንዲቋቋም እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በይፋ እንዲታወጅ ምክንያት ሆነዋል። በዚህ ከፍተኛ ወታደራዊ ባህሪያት ባሉት አጠቃላይ ድባብ ውስጥ የምርጫው ቀን አገሪቱ በግጭትና ባለመረጋጋት ውስጥ ሆና ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የምታደርገውን ጥረት የሚፈትንና የሚያረጋግጥ አጋጣሚ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ የጸጥታ ኃይል መኖሩ ከባቢ ሁኔታው ነጻ እና ለሚዛናዊ ፉክክር ምቹ መሆኑን ከማረጋገጥ እና የጨዋታ ሜዳውን የተስተካከለ ከማድረግ አንጻር የሚፈጥረው ተግዳሮት ይኖራል። ከፍተኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች በእስር ላይ መሆናው እንዲሁም ምናልባትም በሺህ የሚቆጠሩ ደጋፊዎቻቸው መታሰራቸው ውጥረቱን ይበልጥ እያባባሰው እና ምርጫው በሚኖረው ፉክክር ላይ እንዲሁም በኢትዮጵያ ዜጎችን ተሳትፎ መጠን ላይ ተጽእኖ በማሳደር ላይ ይገኛል።

ምንም እንኳን በ2012 ዓ.ም. አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ-ምግባር ሰነድ በመፈረም ከግጭት እና ከማዋከብ ለመቆጠብ ቃል የገቡ ቢሆንም ትግበራው ደካማ መሆኑ እንዲከበር የሚያበረታታ አይደለም። በቅድመ-ምርጫ ሂደት ወቅት ሁለት የኢዜማ እና የአብን ዕጩዎች በኦሮሚያ ክልል እና በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል በድንገት መገደላቸው ተዘግቧል። በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል አንድ የምርጫ ምዝገባ እና የምርጫ ጽ/ቤት ነበር ተብሎ የሚታሰብ ህንጻ መቃጠሉ ተዘግቧል። የልዑካን ቡድኑ ከሰማቸው ሪፖርቶች መካከል በአማራ ክልል ለህዝባዊ ተቃውሞ አደባባይ የወጡ አካላት የብልጽግና ፓርቲ ፖስተሮችን እና ባነሮችን ማውደማቸው ተነግሯል፤ አንዳንድ ፓርቲዎች የአካባቢ ጽህፈት ቤቶቻቸውን እንዳይከፍቱ መስተጓጎል ደርሶባቸዋል፤ እንዲሁም ሴት ዕጩዎችን ጨምሮ በደቡብ ክልል ያሉ አንዳንድ ፖለቲከኞች ለእስር ተዳርገዋል።

በኢትዮጵያ በፌዴራል መንግስት እና በክልል የጸጥታ ኃይሎች መካከል የቅንጅት ማነስ መኖሩን የልዑካን ቡድኑ ካነጋገራቸው አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ለመረዳት የቻለ ሲሆን ይህም በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የጸጥታ ችግሮችን ለመፍታት እና በምርጫው ዕለት እና በምርጫው ማግስት ሰላምን ለማረጋገጥ ስለሚኖረው አቅም ከፍተኛ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ነው። በኮቪድ-19 ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መኖራቸው እና በርካታ ድምጽ መስጠት የሚችል ህዝብ ቁጥር መኖሩ በእራሱ ለሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ሽፋን ከመስጠት አንጻር ለጸጥታ ኃይሎች ተግዳሮት ሊፈጥር ይችላል። ይህ በተለይም ደግሞ በአፋር እና ሶማሌ ክልሎች መካከል የይገባኛል ጥያቄዎች በተነሱባቸው ስፍራዎች፣ እንዲሁም በወታደራዊ የኦፕሬሽን ስራዎች ምክንያት በመቶ ሺህ ሚቆጠሩ ዜጎች በተፈናቀሉባቸው እና ከፍተኛ የግጭት እምቅ አቅም ባለባቸው ጉሙዝ ውስጥ በሚገኙት የመተከል እና የቤንሻንጉል አካባቢዎች የሚስተዋል ነው። በሀገር ውስጥ ያለው የዜጎች መፈናቀልም የመምረጥ መብታቸውን ለማረጋገጥ ጥረት በማድረግ ላይ ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ተግዳሮትን የሚፈጥር ነው።

መንግስት ግጭቶችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ሀብት የመደበ ሲሆን ብሄራዊ የምርጫ ደህንነት ግብረ-ሀይል በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው። ይህ ግብረ ሀይል በውስጡ ካካተታቸው አካላት መካከል ፌዴራል ፖሊስ፣ ብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ መከላከያ ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተወከሉ ሰራተኞች እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባለስልጣኖች ይገኙበታል። ምንም እንኳን ከምርጫ ጋር የተያያዙ ሁከቶችን ለመቅረፍ ሕጎች እና መዋቅሮች የተቀመጡ ቢሆንም እነዚህን ሕጎች የመተግበሩ ሥራ ገና በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ወቅት በርካታ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምርጫ ግጭቶችን ለመከላከል ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ። ሆኖም ግን በርካቶቻቸው ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚያስችል በቂ ሀብት፣ ተደራሽነት እና ልምድ የላቸውም። ስጋት ሊፈጥሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በጊዜ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል በምርጫ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች በቶሎ ምላሽ የመስጫ ሥርዓትን ባካተተው ከምርጫ ጋር የተያያዘ ግጭት መከላከያ መድረክ (JEPP) ውስጥ ሲቪሉ ማህበረሰብ መሳተፉ እንደ አዎንታዊ እርምጃ የሚታይ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ግልጽነትን በማጠናከር እና በጸጥታ ተቋማት ላይ ህዝቡ ያለውን እምነት እና የመተማመን ስሜት በመገባት ረገድ ከጸጥታ ተቋማት ጋር ግንኙነት ማድረግ እና መተባበር ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ነው። የጸጥታ ተቋማት የፖለቲካ ገለልተኝነት ከማሳየት ጎን ለጎን ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን መቻል በምርጫ፣ በቅድመ ምርጫ እና በድህረ ምርጫ ወቅት እጅግ ወሳኝ ነው።

ምርጫው ምን ያህል ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ተደርጎ ይታያል የሚለውን የሚወስነው አንደኛው ጉዳይ በምርጫው ዕለት በሀገሪቷ ውስጥ የሚኖረው የጸጥታ ሁኔታ ይሆናል። ፌዴራል መንግስት እና የክልል ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች የህዝቡን ስጋቶች ለመፍታት እርስ በእርስ ተቀናጅተው እና ተግባብተው ይሠራሉ ወይስ አይሰሩም የሚለው ለወደፊት የሚታይ ይሆናል። የምርጫው ዕለት እና ከዚያ ቀጥሎ ያለው ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተዋንያን ከወገንተኝነት ነጻ መሆናቸውን የሚያሳዩበት እና የዜጎችን የጸጥታ ፍላጎቶች ለማሟላት ምላሽ ሰጪ የሆኑ ስትራቴጂዎችን የሚቀርጹበት ወሳኝ ወቅት ነው፤ እንዲሁም የዜጎችን ደህንነት በሚያረጋግጡበት ወቅት የዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይጣሱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

# ኮቪድ-19 እና የምርጫው ሒደት

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምርጫው ከሚደረግበት ጊዜ፣ ከህዝብ ደህንነት እና ከባለድርሻ አካላት ሚና አንጻር በኢትዮጵያ የምርጫ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። መራጮች፣ እጩዎች እና ደጋፊዎች፣ የምርጫ ኃላፊዎች፣ ሲቪል ማህበራት፣ አክቲቪስቶች እና የምርጫ ታዛቢዎች ሁላቸውም በሂደቱ ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲሳተፉ የሚያስችል ከባቢ ሁኔታን መፍጠር ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ነው። ይህንን ወረርሽኝ መዋጋትን እና የዜጎችን ነጻነቶች ማረጋገጥን አመጣጥነው ጎን ለጎን ማስኬድ ይኖርባቸዋል። የህዝብ ደህንነትን ለማረጋገጥ እና ዲሞክራሲያዊ ምርጫን እውን ለማድረግ አካባቢያዊ እውነታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ግድ ይላል። በተጨማሪም ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዙ የደህንነት ደንቦች የተነሳ አንድም ፓርቲ ወይም እጩ ያልተገባ ጥቅም እንዳያገኝ ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ 200,000 ሰዎች በኮቪድ መያዛቸው እና በግምት 3,000 የሚሆኑ ሰዎች መሞታቸው ሪፖርት ተደርጓል። የበይነ መረብ የምርጫ ግምገማ ተልዕኮው በተከናወነበት ወቅት በኮቪድ-19 የተያዙ ሰዎች ቁጥር በመጨመር ወረርሽኙ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከፍተኛው ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን መጋቢት 30 ላይ 2,121 አዲስ ሰዎች በበሽታው መያዛቸው ተረጋግጧል። በኮቪድ-19 ምክንያት የሞቱ ሰዎች ቁጥርም ትንሽ ቆይቶ ከፍተኛው ደረጃ ላይ በመድረስ ሚያዚያ 10 ቀን 35 ሰዎች ህይወታቸው አልፏል። በበሽታው እንደአዲስ የተያዙ እና የሞቱ ሰዎች ቁጥር ከዚያ ወዲህ መቀነስ አሳይቷል። መጪውን ጊዜ በምንመለከትበት ጊዜ በኦርቶዶክስ አማኞች የፋሲካ በዓል እና በሙስሊሞች የኢድ አል ፈጥር በዓል ወቅት ሚያዝያ/ግንቦት ወር ላይ ሊጨምር ይችላል። በተጨማሪም፣ የኮቪድ-19 መረጃው በበሽታው የተያዙ እና የሞቱ ሰዎችን ቁጥር አሳንሶ ሊያሳይ ይችላል። ለዚህም ምክንያቱ በሀገሪቷ ውስጥ ትክክለኛ የህክምና መረጃ ከማግኘት ጋር በተያያዘ ችግሮች ስላሉ ነው። ኢትዮጵያ ካላት 110 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ ለ20 በመቶው እ.ኤ.አ. እስከ የ2021 መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ክትባት ለመስጠት እቅድ እና ተስፋን የሰነቀች ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ክትባት ያገኙት 2.2 ሚሊዮን ሰዎች ብቻ ናቸው። ምርጫው የሚደረገው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በበሽታው በተያዘበት እና ጥቂቶች ብቻ ክትባት ባገኙበት ሁኔታ ውስጥ እንደሚሆን ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ምርጫ በመደበኛነት በየአምስት ዓመቱ የሚደረግ ስለነበር በ2012 ዓ.ም. እንደሚደረግ ዕቅድ ተይዞ ነበር። የብሄራዊ እና የክልል የህዝብ ተወካዮች የአገልግሎት ዘመን አምስት ዓመት ነው። ሆኖም የምርጫው ቀን ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲራዘም ተደርጓል። ምርጫው ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀን ተቆርጦለታል። የህብረተሰብ ጤና ቀውስ በመከሰቱ የተነሳ ከነሐሴ 2012 ወደ ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ሊዛወር ችሏል። በተከሰቱት ክስተቶች የተነሳ በትግራይ ክልል የተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ አይደረግም።

የኢትዮጵያ መንግስት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጋራ መራጮችን፣ የምርጫ ሀላፊዎችን፣ እጩዎችን እና ደጋፊዎችን እንዲሁም የሲቪል ማህበራትን ከበሽታው የመጠበቅ ዓላማ ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል አዘጋጅተዋል። ይህም አካላዊ ርቀትን መጠበቅን፣ ማስክ ማድረግን እና የእጅ ሳኒታይዘር/ሳሙና መጠቀምን ያካትታል። በበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ተልዕኮው ወቅት በተበጣጠሰ መልኩ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ የማስክ እና የሳኒታይዘር አቅርቦት እንዲሁም እነዚህን የመከላከያ ዘዴዎች ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታ በመራጮች ምዝገባ ወቅት በተለይም ደግሞ በገጠር አካባቢዎች ውስን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ዝግጅቶች ላይ ጭምብል ማድረግም ሆነ ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ ተግባራዊ አለመደረጉን የሚገልጹ ሪፖርቶች ለልዑካን ቡድኑ ደርሰውታል።

እነዚህ በምርጫው ዕለት ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች የስጋት አመላካቾች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ መራጮች ብቻ ሳይሆኑ በምርጫ ጣቢያዎች ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ የፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም የምርጫ ታዛቢዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ በሂደቱ ውስጥ እንዳይሳተፉ ስጋት የሚፈጥር ነው። በተጨማሪም በወረርሽኙ ወቅት ዓለም አቀፍ በረራዎችን ወደ ኢትዮጵያ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ያሉት ተግዳሮቶች (እንዲሁም የጸጥታ ሁኔታው) ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች እንዳይገኙ ሁኔታውን ይበልጥ ያከብደዋል እንዲሁም ለሂደቱ ጥበቃ ከማድረግ እና የምርጫውን አፈጻጸም በተመለከተ ገለልተኛ እና ከወገንተኝነት ነጻ የሆነ መረጃ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የምርጫ ታዛቢ ዜጎች ቀድሞውንም የሚጫወቱትን ቁልፍ ሚና ይበልጥ ያሳድገዋል።

# የምርጫ ማዕቀፍ እና የምርጫ አስተዳደር

## የሕግ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያ ምርጫ የሚመራው በ1987 ዓ.ም በጸደቀው ህገ መንግስት፣ በ2011 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና ስነ-ምግባር አዋጅ፣ በ2011 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመመስረቻ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች ነው[1]። ኢትዮጵያ በርካታ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የምርጫ ደረጃዎችን ተቀብላለች። ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነትን፤ ሁሉንም አይነት የዘር መድልዎ የማስወገድ ስምምነትን፤ በሴቶች ላይ የሚደረግ ሁሉንም አይነት መድልዎ የማስወገድ ስምምነትን፤ እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነትን ያካትታል። በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚ ከሆኑ አህጉራዊ ህጎች መካከልም የአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች እና የህዝቦች መብቶች ቻርተር፤ የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች እና የህዝቦች መብቶች ቻርተር በአፍሪካ የሴቶች መብት ፕሮቶኮል፤ እና የአፍሪካ የዲሞክራሲ እና የምርጫ አስተዳደር ቻርተር ይገኙበታል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት ያወጣውን በአፍሪካ የዲሞክራሲያዊ ምርጫ አስተዳደር ዲክላሬሽን ተቀብላለች።

በ2010 ዓ.ም ኢትዮጵያ የምርጫ ህጎች እና መመሪያዎች ጥናት እና ዳሰሳ ሂደት የጀመረች ሲሆን ይህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ የህግ ማእቀፍን ያካተተ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመመስረቻ አዋጅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችን ሹመት የተመለከተ አዲስ ሥነ-ሥርዓትን፣ የሹመት ቆይታ ዋስትናን፣ የደመወዝ እርከኖችን እና ራሱን የቻለ በጀትን በውስጡ የያዘ ነው። የሹመት ሂደቱን ከዚህ በፊት ከነበረበት የፖለቲካ መድሎ ለማላቀቅ ሲባልም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት የስልጣን ዘመን ወደ ስድስት ዓመት ተራዝሟል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢ በህዳር ወር 2011 ዓ.ም. የተሾሙ ሲሆን ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የሀገር አቀፍ ባለድርሻዎች ከፍተኛ ድጋፍ አላቸው።

በመጪው ምርጫ አማካኝነት ኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ የህግ አውጪ ምክር ቤቱን አባላት የሚመርጡ እና በተዘዋዋሪ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር እና ፕሬዚዳንታቸውን የሚመርጡ ሲሆን የክልል እና ከተማ ምክር ቤቶች ምርጫዎችም በዚሁ ወቅት ይደረጋሉ። የፌዴራሉ ህግ አውጪ አካል ሁለት ምክር ቤቶች በውስጡ አሉት፤ እነሱም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምር ቤት ናቸው።

የሁለቱም ምክር ቤቶች አባላት ለአምስት አመታት የሚያገለግሉ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ብቻ በቀጥታ በህዝብ ድምጽ ይመረጣሉ። በአሁኑ ወቅት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 547 ወንበሮች ያሉት እና ከእነሱም ውስጥ 525 አባላት ከየአንዳንዱ የምርጫ ክልል አንድ በአብላጫ ድምጽ የሚመረጡ ሲሆን 22 ወንበሮች ደግሞ ለአናሳ የህብረተሰብ ክፍሎች የተያዙ ናቸው። የፓርላማ አባላት ምርጫ ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀን ተቆርቶለታል። ግጭት በመኖሩ የተነሳ ለትግራይ ለተመደቡት 38 ወንበሮች ምርጫ አይካሄም። ርዕሰ ብሔር የሆኑት የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት እና የጠቅላይ ሚኒስቴር ሹመት የሚወሰነው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ድምጽ ነው። በአሁኑ ወቅት የፌዴሬሽን ምክር ቤት 153 ወንበሮች አሉት፤ እነሱም ለአስር ክልሎች ተደልድለዋል (የሲዳማ ክልል በ2012 ዓ.ም. በህዝበ ውሳኔ ክልል ሆኗል)። የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት በተዘዋዋሪ መንገድ በክልል ምክር ቤቶች በሚሰጥ ድምጽ ነው። የክልሎችን ምክር ቤት ምርጫን በሚመለከት ከትግራይ ክልል ውጪ የሌሎቹ ምርጫ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ጋር ጎን ለጎን ይደረጋል። በቻርተር የሚተዳደሩት አዲስ አበባ እና ድሬ ዳዋ ከተሞች ሰኔ 5 ቀን 2013 ዓ.ም የከተማ ምክር ቤት ምርጫ ያደርጋሉ። (የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ በሁለቱም ከተሞች ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀጠሮ ተይዞለታል።) የቻርተር ከተሞቹ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ተወካይ የላቸውም።

በምርጫ ሂደት ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት አፈታት ሥርዓቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን፣ የዳኝነት ስርአቱን እንዲሁም ለምርጫው የተቋቋሙ ከተራው ህዝብ የተወጣጡ እና የፓለቲካ ፓርቲዎች ልዩ ኮሚቴዎችን በውስጡ ያካተተ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ የተለያዩ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችል ሰፊ ስልጣን አለው እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲ አባላት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና ይግባኞችን ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል። ከህብረተሰቡ እና ከምርጫ ጣቢያ ሠራተኞች የተወጣጡ አባላት ያሏቸው እና በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶችን በስምምነት የመፍታት ስልጣን ያላቸው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ደረጃ ተቋቁመዋል። በተጨማሪም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተለያዩ ደረጃዎች እንዲሁም ለፍርድ ቤቶች ይግባኝ የሚቀርብበት አሰራር ተዘርግቷል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረኮች በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በአካባቢ ደረጃ ሊፈቱ የሚችሉበት አማራጭ ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን የፓለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ደግሞ በፌዴራል ደረጃ እንደ አማራጭ ያገለግላል። ፍርድ ቤቶች በክልል እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ እንደ ምርጫ የዳኝነት ችሎት ይሰየማሉ፣ በዚህም በምርጫ ሂደት በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ላይ ውሳኔ የመስጠት ሰፊ ስልጣን አላቸው።

በተለያዩ በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ዘዴዎች መካከል ከፍተኛ መደራረብ በስፋት ይስተዋላል፤ በዚህም የተነሳ ባለድርሻ አካላት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለማግኘት ወደ የትኛው አካል መሄድ እንዳለባቸው አውንዲሁም ጉዳዮች የሚፈቱበት መንገድ ፍትሃዊ እና ወጥነት ያለው ስለመሆኑ እርግጠኛ ላይሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። የምርጫ ጣቢያዎች በሁሉም አካባቢዎች ያለመኖራቸው የህግ እውቀት ያላቸው ሰራተኞችን እና የኮሚቴ አባላትን ለመመልመል አዳጋች ስላደረገው እንዳንድ በምርጫ ሂደት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በአካባቢ ደረጃ በተለይም ደግሞ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ላይፈቱ ይችላሉ።

ብዙ ባለድርሻ አካላት አዲሱ የምርጫ ሕግ እና የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወሳኝ የሆኑ ዓለም አቀፍ ደረጃዎች በተሻለ ሁኔታ የሚከበሩበት ሂደት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ ብለው ያስባሉ። ቀድሞ የተሸጋሸገው የምርጫ ቀን እና ምርጫ የሚደረግበትን የጊዜ ሰንጠረዥ ለማክበር ያለመቻሉ መራጩ ህዝብ በምርጫው ሂደት ላይ ያለውን አመኔታ ይቀንሱታል የሚል ስጋት እንዳለባቸው አንዳንድ የመረጃ ምንጮች ገልጸዋል።

## የምርጫ አስተዳደር

በህዳር ወር 2011 ዓ.ም. የቀድሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር እና የፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩት ብርትኳን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነው ተሹመዋል። በፖለቲካው ውስጥ በሁሉም ወገን ያሉ የፓርቲ አመራሮች፣ አክቲቪስቶች፣ ምሁራን እና የሚዲያ ባለሙያዎች በሙሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነጻ እንደሚሆን ለልዑካን ቡድኑ አስረግጠው ገልጸዋል። በተጨማሪም በአዲሷ ሊቀ መንበር ስር ምርጫ ቦርድ ነፃ እንደሚሆን በአፅንዖት የገለጹ ሲሆን የእሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሌሎች ኮሚሽነሮችንም ጭምር ታማኝነት አድንቀዋል። ሆኖም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቴክኒክ ውስንነቶች ያጋጠሙት መሆኑ እና የጊዜ ሰሌዳውን

---

[1] የምርጫ ሂደትን ከሚያስተዳድሩ ሌሎች ህጎች መካከል በ2011 ዓ.ም. የወጣው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ፤ የዜግነት ትምህርትን እና ግንዛቤን የሚያስተዳድሩ ሕጎች፤ የመገናኛ ብዙሀን እና የመረጃ ተደራሽነት አዋጅ (በቅርቡ የተሻሻለው)፤ በ2012 ዓ.ም. የወጣው የጥላቻ ንግግር እና የሀሰት መረጃ ቁጥጥር አዋጅ፤ ሀሳብን የመግለጽ ነጻነትን የሚያስጠብቁ ሕጎች፤ የወንጀል እና የፀረ-ሽብር ሕጎች፤ እና የፖለቲካ ነጻነቶችን የሚያስተዳድሩ ሕጎች ይገኙበታል። እነዚህ ህጎች በንዑስ ህጎች፣ በአዲሱ አዋጅ ስር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በወጡ 15 መመሪያዎች እና ገና በሂደት ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የተደገፉ ናቸው።

ይህ ክስተት በተለምዶ «የወጣቶች ቁጥር መናር» ተብሎ ይጠራል።

ጠብቆ ስራዎችን ማጠናቀቅ አለመቻሉ ግዴታውን ለመወጣት ስለመቻሉ ስጋትን ፈጥሯል። በ1997፣ በ2003 እና በ2007 የተደረጉት ሀገር አቀፍ ምርጫዎች ከፍተኛ ትችት የቀረበባቸው ሲሆን ይህም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መልካም ስም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ፈጥሯል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አዳዲስ ሰራተኞችን ለመመልመል የወሰነውም በዚሁ የተነሳ ነው። ሆኖም ግን እነዚህ ሰራተኞች አብዛኞቹ የምርጫ አስተዳደር ልምድ ይጎድላቸዋል። ስለሆነም ሀገር አቀፍ ምርጫው በመከናወን ላይ እያለ ለእነዚህ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ሆኗል። እየሰሩ መማር የሚለው አካሄድ አልፎ አልፎ የሚደገፍ ቢሆንም የፊታችን ግንቦት የሚደረገውን ምርጫ ይበልጥ ውስብስብ ሊያደርገው ይችላል።

የምርጫ አስተዳደሩ የሚከተሉት ሦስት እርከኖች አሉት፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤቶች፣ 673 የምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች እና 41,710 የምርጫ ጣቢያዎች (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕቅድ 99 የዞን ማስተባሪያ ጽ/ቤቶችን ያካትታል)። በአዲስ መልክ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አምስት ቋሚ የቦርድ አባላት እና አንድ ጽ/ቤት አሉት። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመላው ሀገሪቷ አንድ ወጥ የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤቶችን ለመመስረት አቅዶ የነበረ ቢሆንም ይህን በጊዜ ሰሌዳው መሰረት ለማከናወን ሳይችል ቀርቷል። በዚህም ምክንያት ከምርጫ የጊዜ ሰሌዳው አንጻር ብዙ ስራዎች ዘግይተዋል። ይህም የምርጫ የጊዜ ሰሌዳውን ከማክበር አንጻር ብዙ መዘግየቶችን ያስከተለ ሲሆን ከእነዚህ ዘግየቶች ውስጥም አንዳንዶቹ በግልጽ ለህዝብ ይፋ አልተደረጉም።

በኢትዮጵያ የመራጮች መዝገባ በተነቃቃ ሁኔታ በመከናወን ላይ ያለ ሲሆን ምንም እንኳን መዘግየቶች ቢኖሩም ከምርጫው አስቀድሞ የሚጠናቀቅ ይሆናል። በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ የተያዘለት ከየካቲት 22 እስከ መጋቢት 21 እንዲከናወን የነበረ ቢሆንም ኋላ ላይ ወደ ከመጋቢት 16 እስከ ሚያዚያ 15 ተቀይሯል። ሚያዚያ 15 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሂደቱ እስከ ሚያዝያ አጋማሽ ካልተጀመረባቸው አካባቢዎች ውስጥ በሚጠቀሱት በአፋር እና ሱማሌ ክልሎች የመራጮች ምዝገባን ለሶስት ሳምንታት እስከ ግንቦት 6፤ እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በሁለት ሳምንት እስከ ሚያዝያ 29 ቀን አራዝሟል። ከዚያም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባ ለተጨማሪ አንድ ሳምንት እስከ ግንቦት 6 ድረስ መራዘሙን ይፋ አድርጓል። እነዚህ ለውጦች ዘግይተው ይፋ በተደረጉበት ወቅት ሌሎች መዘግየቶች ይኖራሉ የሚሉ ሰፊ ግምቶች ነበሩ። ሚያዝያ ወር መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከምርጫ ጣቢያዎች ግማሽ የሚሆኑት ብቻ በስራ ላይ መሆናቸውን እና መራጮችን መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን ይፋ አድርጓል። አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች አንደጠቆሙት በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች በቂ አገልግሎት አላገኙም፤ አንዳንዶች ደግሞ በተለይ ወጣቶች እና የመጀመሪያ ጊዜ መራጮች በሁኔታው ደስተኛ እንዳልሆኑ ጠቁመዋል።

የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር መጀመሪያ ላይ ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን ይህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ማህበረሰቡን ይበልጥ በማስተማር እና በመቀስቀስ እንዲሁም የሚያዚያ ወር አጋማሽ ላይ ቅስቀሳ በማድረግ ህዝቡን እንዲመዘገብ እንዲያበረታቱ አነሳስቷቸዋል። የመገናኛ ብዙሀን ዘገባዎች እንደገለጹት ከሆነ ፌዴራል መንግስቱ የመራጮች ምዝገባን በማሳለጡ ሥራ ውስጥ ክልሎችን አሳትፏል። ይህ ህዝብን ለምርጫ የማነሳሳት እና የማንቀሳቀስ ሥራ በይበልጥ አሁን ስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ሊመርጡ ወደሚችሉ ሰዎች ሊያደላ ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። በሚያዚያ ወር መጨረሻ አካባቢ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 41,000 የሚሆኑ የመራጮች ምዝገባ ማዕከላት በስራ ላይ መሆናቸውን እና በቀጣዮቹ ቀናትም ቁጥራቸው እየጨመረ መሄዱን ይቀጥላል ተብሎ እንደሚጠበቅ ለቅድመ ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድኑ አሳውቋል።

የመራጮች ምዝገባ አሀዞችን ለህዝብ ከማሳወቅ ጋር የተያያዙ ድክመቶች መኖራቸው እና የመራጮች ቁጥር በድንገት ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየቱ፤ በዚህም እስከ ሚያዝያ 15 ደረስ ከ20 ሚሊዮን በላይ መራጮች መመዝገባቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸው፤ በምርጫው ተአማኒነት ላይ ጥርጣሬዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የህዝብ ግንኙነቱ ውስን ከመሆኑ እና የምርጫ ታዛቢ ዜጎች ሂደቱን የማይታዘቡት ከመሆኑ ጋር ተያየይዞ በርካታ መገናኛ ብዙሀን እና የክልል መንግስታት ተወካዮች የሚያወጧቸውን ቁጥሮች ለማረጋገጥ አልተቻለም፤ ይህም በተጨባጭ የመራጮች ምዝገባ የሚገኝበትን ደረጃ በተመለከተ የተለያዩ መላ ምቶች እንዲሰነዘሩ ምክንያት ሆኗል፤ እንዲሁም አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እንደሚሉት ከሆነ መራጮች በምርጫው ላይ ያላቸውን እምነት የሚሸረሽር ነው። ከዚህም ባሻገር መረጃ በግልጽ ለህዝብ ተደራሽ ያለመደረጉ ስለ ሂደቱ አካታችነት ጥያቄዎች እንዲነሱ እና ስለ አዲሶቹ ህግ አውጪዎች ስጋቶች እንዲቀሰቀሱ አድርጓል። በተጨማሪም የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ ከመጠናቀቁ አስቀድሞ የምርጫ ካርዶች መታተማቸው መገለጹ በአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ዘንድ በምርጫው ዕለት ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ስለመዘርጋቱ ጥርጣሬን ፈጥሯል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለጸው የተለያዩ መዘግየቶች ያጋጠሙ ሲሆን ለዚህም በከፊል መንስኤ ናቸው ከተባሉት መካከል ማቴሪያሎችን ከማጓጓዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ በፌዴራል እና በክልል አስተዳደር አካላት መካከል በተለይም ደግሞ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምዝገባ መዘግየት ጋር በተያያዘ ደካማ ቅንጅት መኖሩ፣ ጥራት ያላቸው ባለሙያዎችን ከመሳብ እና በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ከማሰራት ጋር በተያያዘ ያሉ ክፍተቶች እንዲሁም በተለያዩ የክልል አካባቢዎች የጸጥታ ሁኔታው እየተባባሰ መሄዱ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ቅሬታዎች በተለያዩ ታዛቢዎች የተገለጹ ናቸው።

በተጨማሪም በተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች ላይ የሚደርስ ማስፈራራት እና እስር በአንዳንድ አካባቢዎች መራጮች ለመመዝገብ ያላቸው ፍላጎት እንዲቀንስ ምክንያት እንደሆነ አስተያየተት ሰጪዎች በዝርዝር ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል እና በአማራ ክልል አንዳንድ እጩዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል። በኦሮሚያ ክልል የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች መታሰራቸው ቢያንስ ሁለት ፓርቲዎች በምርጫው ሂደት ላይ እንዲያድሙ ምክንያት ሆኗል፤ ይህም አንዳንድ አስተያየት ሲዎች እንደሚሉት ከሆነ በሀገሪቷ ከፍተኛው የህዝብ ቁጥር ባለው በኦሮሚያ ክልል የመሳተፍ ፍላጎት እንዲቀንስ አድርጓል። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች በመራጮች ዘንድ ፍላጎት ማጣት እንደሚስተዋል እና ለዚህም በከፊል ምክንያቱ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ምርጫውን ያሸንፋል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ይህም ከጸጥታ እና ከኢኮኖሚ ችግሮች ጋር ተደምሮ ለበርካታ ኢትዮጵያዊያን የመምረጥን አስፈላጊነት ጋርዶባቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአምስት ቋንቋዎች በብሮድካስት ሚዲያ እና በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ለህዝብ ማስታወቂያዎችን በማውጣት በመራጮች ምዝገባ እና በምርጫ ዕለት በሚኖረው ሥነ-ስርዓት ዙሪያ የመራጮች ስልጠና መስጠት ጀምሯል። ሆኖም ግን አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እነዚህ ጥረቶች ያለውን ፍላጎት እንዳላሟሉ ይገልጻሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚሰራጩ ማቴሪያሎችን አዘጋጅቷል። የመራጮች ስልጠና ማቴሪያሎች የተሰራጩ ሲሆን አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ማቴሪያሎች እና መልእክቶች በሌሎች ተጨማሪ ቋንቋዎች እንዲቀርቡ ጥያቄ አቅርበዋል። ምንም እንኳን እነዚህ ጥረቶች አዎንታዊ ተደርገው የሚታዩ ቢሆንም የመራጮችን የመረጃ ፍላጎት ለማርካት በቂ እንዳልሆኑ አንዳንድ ታዛቢዎች ይገልጻሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድኑ ያነጋገራቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሂደቱን የማስተዳደር እና የጊዜ ሰሌዳውን የማክበር አቅም በአብዛኛው ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሁኔታዎች የሚወሰን እንደሆነ ገልጸዋል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ለመስጠት የምክክር አካሄድን እየተከተለ እንደሆነ እና የተቃዋሚዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ድጋፍ ለማግኘት ጥረት እያደረገ እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ።

ከዚህ ጎን ለጎን በርካታ አስተያየት ሰጪዎች አንዳንድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎችን እንዲሁም በተለይም ደግሞ በእስር ላይ ያሉ ሰዎች መመዝገብ አለመቻላቸውን እና ከፖለቲካ እና ከቅስቀሳ የገንዘብ ድጋፍ ስርጭት ጋር በተያያዘ መዘግየቶች መኖራቸውን የተቹ ሲሆን ይህም በተለይ አነስተኛ የሆኑ እና በአንጻሩ ውስን ሀብት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይበልጥ የሚጎዳ እንደሆነ ይነገራል። ይህ በተለይም በሱማሌ ክልል የክልሉ የምርጫ አስተዳደር አካላት ወገንተኛ የመንግስት ሰራተኞች ናቸው በሚል በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች በምርጫው እንዲያድሙ ምክንያት ሆኗል።

የበይነ መረብ የቅድመ ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድኑ ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎች በምርጫው ዕለት የምርጫ ውጤቶች ከምርጫ ጣቢያዎች ስለሚተላለፉበት መንገድ ስጋቶች እንደሏቸው ገልጸዋል። እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውጤቶችን በፍጥነት፣ በጥንቃቄ እና በግልጽነት ለፓርቲዎች፣ ለእጩዎች እና በተለይም ለህዝቡ በማስተላለፍ በመጨረሻው ውጤት ላይ እምነት ለመፍጠር ጥረት ሊያደርግ ይገባል። ይህም በተለይ አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት በ1997 ዓ.ም. ምርጫ የውጤት ቆጠራ ሂደት ላይ ህዝቡ ሰፊ ጥርጣሬ የነበረው በመሆኑ እና የምርጫው ውጤት ከተሰጠውን ድምጽ ብዛት ጋር የሚጣጣም አይደለም የሚል ከፍተኛ ስጋት ስለነበረ ነው።

# የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የቅስቀሳ የጊዜ ሰሌዳ

የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት የተመዘገቡ ብሔራዊ እና ክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ግዴታዎች በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣው መመሪያ መሰርት ይመራል፣ ይህም በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ አዋጅ ላይ የተመሠረተ ነው። በወቅቱ የፖለቲካ እና የምርጫ መሻሻያ መሰረት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫ እንደገና መመዝገብ አለባቸው። ይህንንም ለማድረግ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ የሀገራዊ ፓርቲ መስራች አባላት ቢያንስ የ10,000 ደጋፊዎችን ፊርማ እንዲሰበስቡ የሚያስገድድ ቅድመ ሁኔታ የሚገኝበት ሲሆን ከእነሱም ውስጥ ከ40 በመቶ ያላነሱት የአንድ ክልል ነዋሪዎች ሊሆኑ ይገባል። ክልላዊ ፓርቲዎች ቢያንስ የ4,000 ደጋፊዎችን ፊርማ እንዲሰበስቡ የሚያስገድድ መስፈርት ያለ ሲሆን ከእነዙም ውስጥ ቢያንስ 60 በመቶው የዚያው ክልል ቋሚ ነዋሪ ሊሆኑ ይገባል።

የልዑካን ቡድኑ ያነጋገራቸው በርካታ አስተያየት ሰጪወዎች የፊርማ መስፈርቱ እጅግ የበዛ መሆኑን እንዲሁም አነስተኛ የክልል ፓርቲዎች ውስን ሀብት ያላቸው በመሆኑ አዳጋች እንደሆነባቸው ገልጸዋል። አንዳንዶች ደግሞ ፊርማዎችን የማረጋገጥ ሂደቱ ታማኝነት ላይ ጥያቄዎችን ያነሳሉ። ከእነዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና በርካታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አልተመዘገቡም። ከእነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ ሁለቱ፤ ማለትም የኦሮሚያ ዲሞክራሲያዊ ጥምረት እና ገዳ ስርአት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘግይቶ በሰጠው ውሳኔ መሰረት በመጪው ምርጫ ላይ መሳተፍ አይችሉም። ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች እንዲሁም አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አድማቸውን ለመግለጽ ከሂደቱ እራሳቸውን በማግለላቸው የተነሳ በርካታ አስተያየት ሰጪዎች በአንዳንድ አካባቢዎች ምርጫው ፉክክር ያለበት ስለመሆኑ ጥያቄ ያስነሳሉ። ውስን አማራጭ በመኖሩ ወይም አንዳንድ ፓርቲዎች ባለመሳተፋቸው የተነሳ ስለ መራጮች ተሳትፎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

የእጩዎች የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ከየካቲት 08 እስከ የካቲት 21 ድረስ እንዲሆን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በአጭር ማስታወቂያ እስከ የካቲት 30 ተራዝሟል። አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩዎቻቸው በግል ቢያንስ 3,000 ፊርማዎችን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልላቸው ውስጥ ካሉ መራጮች በድጋሚ እንዲሰበስቡ እንደተጠየቁ በመግለጽ ቅሬታቸውን አሰምተዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ 9,000 እጩዎች 46 ፓርቲዎችን በመወከል ይወዳደራሉ፣ እንዲሁም 125 የግል ተዋዳዳሪዎች ተመዝግበዋል። እነዚህ እጩዎች ለመራጮች አማራጭ የሚሆኑ ቢሆንም አንዳንድ ፓርቲዎች እጩዎቻቸው በአንዳንድ አካባቢዎች ቅስቀሳ ለማድረግ የደህንነት እና የጸጥታ ስጋት እንዳለባቸው እና ይህም የፈለጉትን ያህል የምርጫ ክልሎች ላይ ዕጩዎችን እንዳያስማሩ እንደከለከላቸው ቅሬታቸውን አቅርበዋል። ከላይ እንደተገለጸው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) እና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) አመራሮቻቸው እና አባላቶቻቸው በመታሰራቸው እና ትንኮሳ የደረሰባቸው በመሆኑ በምርጫው እንደማይሳተፉ አሳውቀዋል። በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ሌሎች በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች እንዲሁም የተለያዩ ፓርቲዎች አባላት አሁንም ድረስ በእስር ላይ ይገኛሉ፤ እንዲሁም በእጩነት ለመመዝገብ አልቻሉም።

እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የእያንዳንዱን አካባቢ የእጩዎች ዝርዝር ለማሳተም አልቻለም፤ ይህም በምርጫውን አጠቃላይ ግልጽነት ላይ ጥያቄ አስነስቷል እንዲሁም በተለይም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አንድ ተወካይ ባላቸው አንዳንድ የምርጫ ክልሎች ፉክክር አይኖርም የሚል ጥርጣሬን ፈጥሯል። ለፓርላማ እና ለክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ብልጽግና ፓርቲ 2,432 እጩዎችን እንዳስመዘገበ እንዲሁም ኢዜማ 1385 እጩዎችን፣ እናት ፓርቲ 573 እጩዎችን እና አብን 491 እጩዎችን እንዳስመዘገቡ የኢትየጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መጋቢት 2 ይፋ አድርጓል። የኢትየጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፌዴራል/ክልል እጩዎችን ከፋፍሎ እንዲሁም የዕጩዎችን የጾታ ስብጥር ይፋ አላደረገም።

በታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም. የኢትየጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ ባደረገው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቅስቀሳ የጀመረው የካቲት 8 ነው። ሆኖም አንዳንድ ፓርቲዎች ቅስቀሳ የጀመሩት ዘግይተው ነው፤ በጸጥታ ችግር ምክንያት ቅስቀሳቸው እየተስተጓጎለባቸው ያሉ ፓርቲዎችም አሉ። በርካታ ፓርቲዎች የጤና ሚኒስቴር ያወጣቸውን ፕሮቶኮሎች ባልተከተለ መልኩ ቅስቀሳዎችን በማድረግ እና በአካል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ላይ ሲሆኑ ይህም የምርጫው ዕለት እየተቃረበ ሲመጣ የወረርሽኙ ስርጭት የመጨመሩን ዕድል ከፍ ያደርገዋል። በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ሱማሌ እና አፋር ክልል ያለው ያለመረጋጋት ፓርቲዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ ቅስቀሳ ማድረግ ስለመቻላቸው ጥያቄ እያስነሳ ይገኛል። ይህም ምርጫው ፉክክር ያለበት መሆኑንም እንዲሁ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው።

ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እና የምርጫ ታሪክ በመነሳት የምርጫ መወዳደሪያ ሜዳው ፍትሃዊነት ተጽዕኖ አድሮበታል ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን ኢህአዴግ የፈረሰ ቢሆንም የፓርቲ መዋቅሮቹ እና በሀገሪቱ ላይ ያለው ቁጥጥር አሁንም እንደቀጠለ ነው። በእርሱ ቦታ ለተተካው ብልጽግና ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች የተሻለ ዕድል የሚፈጥሩለት ሁኔታዎችም አሉ። የብልጽግና ፓርቲ ባለው የድርጅታዊ መዋቅር ደረጃ፣ በሀብቱ እና በማዳረስ ተወዳዳሪ የለውም። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ፓርቲው የመንግስት ህንጻዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ያለአግባብ ለቅስቀሳ እየተጠቀመ ነው ሲሉ ይደመጣሉ። ከኢዜማ በስተቀር በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕጩዎችን ለማሰማራት አቅሙ እና ሀብቱ ያላቸው ፓርቲዎች በጣም ጥቂት ናቸው። አንዳንድ የክልል አስተዳደሮች የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ቅስቀሳ ያስተጓጎሉ ሲሆን ይህም በሂደቱ ተአማኒነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

ኦፌኮ እና ኦነግ አድማቸውን ለመግለጽ ከምርጫው ራሳቸውን ማግለላቸው በምርጫው ሂደት ውስጥ ፉክክር እንዳይኖር እንቅፋት ይሆናል። ሁለቱም ፓርቲዎች በህዝብ ቁጥር በኢትዮጵያ ትልቁ ክልል በሆነው በኦሮሚያ ክልል ፖለቲካ ውስጥ ያላቸው ተጽእኖ አሁንም የቀጠለ ሲሆን ይህም በኦሮሚያ መራጮች በምርጫው ቀን ከፖለቲካ አንጻር የሚኖሯቸውን አማራጮች በተመለከተ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው። ስለሆነም በኦሮሚያ ክልል በምርጫው ዕለት በጣም ውስን አማራጮች መኖራቸው በሕዝብ ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል እና ከምርጫው ራስን የማግለል አድማው የፀጥታ ችግር ሊፈጥር ይችላል የሚለው ፍርሀት ድምፅ የሚሰጡ ሰዎችን ቁጥር ሊቀንሰው እንደሚችል በርካታ ባለድርሻ አአካላት ይጠቁማሉ። በህዝብ ቁጥር ሁለተኛው ትልቅ ክልል በሆነው የአማራ ክልል አንዳንድ ከተሞች ሰፊ ህዝባዊ ተቃውሞዎች መደረጋቸው ሪፖርት የተደረገ ሲሆን በተለያዩ ዞኖች ያለው የጸጥታ ሁኔታ ባለፉት ሳምንታት ውስጥ ተባብሷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአማራ ክልል ግጭት ቀስቃሽ ቋንቋ ተጠቅመዋል በማለት ለብልጽግና ፓርቲ እና ለአብን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። በሱማሌ ክልል የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ)፣ ኢዜማ እና ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ) ከሌሎች የግል እጩዎች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በክልሉ ያለው የመራጮች ምዝገባ አሠራር ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ከሚያዝያ 11 ጀምሮ የምርጫ እንቅስቃሴዎችን አቋርጠዋል። በተጨማሪም በትግራይ ምርጫ የማይደረግ እና በክልሉ የተቋቋሙ ድርጅቶች በምርጫ ሂደቱ ተሳታፊ የማይሆኑ ሲሆን ይህም በሌሎች ክልሎች መራጮች የሚኖሯቸውን አማራጮች ውስን ሊያደርግ የሚችል ነው።

የምርጫ ዘመቻ መልእክቶቹ የኑሮ ውድነትን እና ስራ አጥነትን፣ የብሔር ግጭትን እና ጸጥታን እንዲሁም በተወሰነ መልኩ የፓርቲ መድረኮችን እና ርዕዮተ-ዓለምን የሚመለከቱ ናቸው። በአሮጌው እና በአዲሱ የፖለቲካ ስርዓት መካከል ያለው ልዩነት በምርጫ ቅስቀሳ መልዕክት ውስጥ፤ በተለይም ደግሞ የብሔር ፌዴራሊዝምን መሰረት ያደረገው ነባሩ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ይቀጥል ወይስ አሃዳዊ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ህገ-መንግስት ይኑር የሚሉትን ጉዳዮች በተመለከተ በግልጽ ይስተዋላል።

# የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ

ከ2010 ዓ.ም ወዲህ ለብዝሃነትን አስፈላጊነት ዕውቅና ከመስጠት እና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን በፖለቲካ ህይወት ውስጥ ከማካተት አንጻር ግልጽ መሻሻሎች ተስተውለዋል። በመንግስት ከፍተኛ ሹመቶች፣ በሕግ ማዕቀፉ ላይ የተደረጉ ለውጦች እና በንግግር ዘይቤ ላይ የታዩ ለውጦች ሁሉም በዚህ ረገድ አዎንታዊ ምልክቶች ናቸው። ሆኖም ከእነዚህ ለውጦች ጎን ለጎን ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ በቁጥር አናሳ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ሌሎች የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢትዮጵያ በአደባባይ ህይወት ውስጥ በአጠቃላይ እንዲሁም በተለይም ደግሞ በምርጫ ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ ያላቸውን አቅም የሚገድቡ ስር የሰደዱ ልማዶች አሁንም እንደቀጠሉ ነው። በሀገሪቷ ውስጥ የጸጥታ ችግር መኖሩ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸውን ተሳትፎ በአንጻሩ በከፍተኛ ሁኔታ ይገድባል እንዲሁም በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በሚካተቱ ሴቶች ላይ ይብልጥ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው። በተጨማሪም ለተሳትፎአቸው እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች እና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች መወከላቸውን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ አዎንታዊ እርምጃዎች አፈጻጸም በይፋ ከሚደረጉ ንግግሮች አንጻር ወደ ኋላ ቀርተዋል።

የሴቶች የምርጫ ተሳትፎ የሚከናወነው ወንድን የበላይ አድርገው በሚያዩ ልማዳዊ አስተሳሰቦች እና መጠነ ሰፊ ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በሚፈጸሙበት ሰፊ አውድ ውስጥ ነው። አሁን ያሉት የኢትዮጵያ ፕሬዝደንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀመንበርን ጨምሮ በርካታ ሴቶች መሾማቸው ፖለቲካውን አካታች የሚያደርግ እና ሴቶች በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና የሚያሳይ በመሆኑ በአዎንታዊ መልኩ የሚታይ ነው። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥ በብሔራዊ ደረጃ ሴቶች በአንጻሩ በተሻለ የተወከሉ ቢሆንም በክልል ጽ/ቤቶች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ በቂ ውክልና የላቸውም፤ እንዲሁም ሴቶች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ያላቸው ውክልና በክልል ደረጃ ካለው አማካይ የተሻለ (38.8 በመቶ እና 24.1 በመቶ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል) ሲሆን ይህም የኢህአዴግ ኢ-መደበኛ የኮታ ስርአት ያስገኘው ውጤት ሊሆን ይችላል።

ምንም እንኳን ዕጩዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ የሌለ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሴቶች ተሳትፎ ከዚህ ቀደም ከነበረው ጋር የሚወዳደር እንደሚሆን ለበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድኑ የገለጸ ቢሆንም በርካታ አስተያየት ሰጪዎች የሴት ዕጩዎች ቁጥር እንዲሁም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ሴቶች ያላቸው ውክልና ቀንሷል ብለው ያምናሉ። በዚህ ረገድ ሴቶች እጩ እንዳይሆኑ ወይም በፓርቲዎቻቸው ውስጥ የአመራር ቦታዎችን እንዳይዙ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውን ለልዑካን ቡድኑ የገለጹ ፓርቲዎች የሉም። ለዚህም ምላሽ ለመስጠት ሲባል የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በምርጫ ሂደት ውስጥ በሴቶች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ማህበሩ ለወሲባዊ እና የጾታ ጥቃት የሚያገለግል ነጻ የስልክ መስመር አለው። እ.ኢ.አ. በ2008 አገልግሎት መስጠት የጀመረው ይህ የስልክ መስመር ገዳቢ የፖለቲካ እና የሕግ ከባቢ ሁኔታ የነበረ በመሆኑ ታግዶ ነበር።

እንደተቀሩት ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ሁሉ በኢትዮጵያ በስነ-ህዝብ ላይ የታዩ ለውጦች የወጣት ዜጎች ቁጥር መጨመርን አስከትለዋል።[2] በኢትዮጵያ ብሄራዊ የወጣቶች ፖሊሲ መሠረት ወጣቶች ማለት ከ15 እስከ 29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች ማለት ሲሆን ከ18 እስከ 29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች ለመምረጥ የሚያስችል የዕድሜ ክልል ውስጥ ካለው የሀገሪቱ ህዝብ ውስጥ 40 በመቶውን ይይዛሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ወጣት መራጮች ከምርጫ ጋር በተያያዘ የነበሯቸው ተሞክሮዎች አካታችነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የላቸውም ተብለው በሰፊው ከተተቹ ምርጫዎች ብቻ ጋር የተያያዙ ነበሩ። ምንም እንኳን ምህዳሩ በአዲስ መልኩ መስፋቱ ወጣቶችን በሂደቱ እንዲሳተፉ ሊያበረታታ የሚችል ቢሆንም የበይነመረብ አጠቃቀማቸው በማህበራዊ ሚዲያ ለሚሰራጭ ሀሰተኛ መረጃ ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል። በርካታ ፓርቲዎች ለወጣቶች ተሳትፎ ትልቅ ግምት ይሰጣሉ እንዲሁም ወጣቶችን በምርጫ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለማሳተፍ እና በተለይም ደግሞ ወጣቶችን ኢላማ አድርገው ለመንቀሳቀስ ልዩ ተነሳሽነት አላቸው። በየዘርፉ ያሉ ፓርቲዎች ለወጣት መራጮች ወሳኝ ለሆኑ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ ለሥራ አጥነት መፍትሄ ያለማቅረባቸውን ቀጥለዋል። ኪዚህ ቀደም የተደረጉ ኢንቨስትመንቶች ይብልጥ የተማረ እና የኢኮኖሚ ዕድሎችን ፍለጋ ወደ ከተሞች የሚሳብ ህዝብን የፈጠሩ ቢሆንም እነዚህ የኢኮኖሚ ዕድሎች በአሁኑ ወቅት አሉ ለማለት አይቻልም። ፓርቲዎች ለነዚህ ጉዳዮች ትኩረት ያለመስጠታቸው ወጣቶች ተስፋ ሊቆርጡ የሚችሉበትን ዕድል በማስፋት በፖለቲካ ውስጥ እንዳይሳተፉ ወይም ከብሔር ጋር የተያያዙ ግጭቶች ተጠቂ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል።

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ወደ አንድ ስድስተኛ አካባቢውን ይይዛሉ። ምንም እንኳን በዚህ መልኩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቢሆንም የአካል ጉዳተኞች በምርጫ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ዝቅተኛ ነው። አዲሱ የምርጫ ህግ በብሬልም ጭምር የተዘጋጀ ቢሆንም የምርጫ ካርዶች እና የመራጮች ስልጠና ማቴሪያሎች በብሬል አልተዘጋጁም። ምንም እንኳን በአንዳንድ የክልል አካላት ውስጥ የመሪነት ቦታዎች ላይ አካል ጉዳተኞች ቢቀመጡም ፓርቲዎች የአካል ጉዳተኞችን ማካተት ላይ እንዳልሰሩ በርካታ ባለድርሻ አካላት ለቅድመ ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድኑ ገልጸዋል። አንዳንድ የአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች በምርጫ ወቅት የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚረዱ ሰፊ ምክረ-ሀሳቦችን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቅረባቸውን እና እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ምክረ-ሀሳቦቹን ታሳቢ ማድረግ አይቻልም የሚል ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል። የመራጭ ምዝገባ የሚከናወነው በትላልቅ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች (እንደ ወረዳ እና ዞን ባሉ ደረጃዎች) ሳይሆን በምርጫ ጣቢያዎች ነው፤ ይህም አካል ጉዳተኞች መጓዝ የሚኖርባቸውን ርቀት በማሳጠር ከመመዝገብ ጋር በተያያዘ የሚኖርባቸውን ጫና ቀንሶት ሊሆን ይችላል። ሆኖም የመራጮች ምዝገባ እጅግ መዘግየቱ፣ በርካታ ጣቢያዎች ዘወትር ክፍት ያለመሆናቸው እና ሂደቱን በተመለከተ በቂ ወቅታዊ መረጃ ያለመሰጠቱ ለምዝገባ ወደተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ከመመላለስ ጋር በተያያዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሳ ለአካል ጉዳተኞች በአንጻሩ ከፍተኛ እንቅፋትን ፈጥሯል።

በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ከሁለት ሚሊዮን ማለፉን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወጡ ግምቶች ያሳያሉ። ከእነዚህም ውስጥ 40 በመቶው ከ18 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው እና መምረጥ የሚችሉ ናቸው። የካምፓላው ስምምነት (እ.ኤ.አ. በ2019 ዓ.ም. ተፈጻሚ መሆን የጀመረው) ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብት ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን ኢትዮጵያም ይህንኑ ስምምነት በየካቲት ወር 2012 ዓ.ም. አጽድቃዋለች። የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣው መመሪያ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የምርጫ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ወስኗል። አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ከሆነ የፌዴራል እና የክልል ባለስልጣን አካላት ንቁ ተሳትፎ ባለማድረጋቸው የተነሳ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን ለማቋቋምም ሆነ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ተደራሽ ለማድረግ አዳጋች ሆኗል። ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ውስጥ አብዛኞቹ ለመምረጥ አልተመዘገቡም እንዲሁም በምርጫው ቀን ለመምረጥ አይችሉም የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ። በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከዜግነት እና ከምርጫ ስልጠና ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ሥራዎችን በተመለከተ በቂ ትኩረት አላገኙም ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም በምርጫው ተሳታፊ የመሆን ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም በምርጫ ሂደት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ግጭቶች ጋር የተያያዙ

---

[2] ይህ ክስተት በተለምዶ «የወጣቶች ቁጥር መናር» ተብሎ ይጠራል።

ስጋቶች ተፈናቃዮችን በምርጫው እንዳይሳተፉ ሊያደርጋቸው ይችላል።

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔሮችን ያቀፈ ብሔርን መሰረት የደረገ ፌዴራል ሥርዓት ያላት ሀገር ናት። ይህም ሂደቱን ሁሉን አካታች ከማድረግ አንጻር ተግዳሮቶችን የሚፈጥር ነው። እስከ 2012 ዓ.ም. ድረስ አማርኛ ብቸኛው ይፋዊ የፌዴራል ቋንቋ ነበር። ሆኖም ግን ከሀገሪቱ ህዝብ ውስጥ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋው የሆነው አንድ ሦስተኛው ብቻ ነው። ኦሮምኛ፣ አፋርኛ፣ ሱማሊኛ እና ትግርኛ በቅርቡ ይፋዊ የፌደራል መንግስት ቋንቋ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ስልጠና ማቴሪያሎችን ወደ እነዚህ ቋንቋዎች ለማስተርጎም ጥረት አድርጓል። ሆኖም እነዚህ ቋንቋዎች የመጀመሪያ ቋንቋቸው ያልሆኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች አሉ። በተጨማሪም ከምርጫ ጋር የተያያዙ በርካታ ሰነዶች እንዲሁም የምርጫ ሕጉ አሁንም ድረስ የሚገኙት በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔረሰቦች በምርጫው ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ተግዳሮት የሚፈጥሩ ናቸው።

# የሲቪል አውዱ እና የዜጎች ተሳትፎ

በ2001 ዓ.ም. ወጥቶ የነበረው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በ2018 ዓ.ም. መሻሩ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱበትን ምህዳር በአዲስ መልኩ ያሰፋላቸው እና በመራጮች እና በሲቪል መብቶች ስልጠና ላይ እንዲሁም ምርጫን በመታዘብ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እንዲሳተፉ እንዳስቻላቸው አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል። ከ190 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ጥምረቶች በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የመራጮች ስልጠና እንዲሰጡ እውቅና ተሰጥቷቸዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለ36 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዕውቅና የሰጠ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በሥርዓተ-ጾታ፣ በአካል ጉዳተኞች እና በተፈናቃዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ሰፊ ጥምረቶች እና ድርጅቶች ይገኙበታል። በተፈጠሩት ሁኔታዎች ምክንያት በሚያሳዝን ሁኔታ የአውሮፓ ህብረት ውስን የምርጫ ታዛቢ ልዑካን ቡድን የማሰማራት ዕቅዱን ለመሰረዝ የተገደደ መሆኑን የቴክኒክ ቡድኑ የተገነዘበ ሲሆን ይህም የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች መኖር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ የሚያስቆጭ ነው።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምርጫ ጥምረት (CECOE) ከ160 በላይ ድርጅቶችን ያካተተ ሀገር አቀፍ ጥምረት ሲሆን የመራጮች ስልጠና እና የዜጎች ምርጫ መታዘብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ጥምረቱ በተለያዩ ቋንቋች እና በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል። “እኔ እመርጣለው” የተሰኘ የመራጮች ስልጠና ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛል። ከታዛቢነት ጋር በተያያዘ ጥምረቱ በህዳር ወር 2012 ዓ.ም. የተካሄደውን የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን ታዝቧል እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ ሂደቱን የሚታዘቡ ሰዎችን አሰማርቷል። በተጨማሪም ግንቦት በሚደረገው ምርጫ ላይ በመላ ሀገሪቱ ታዛቢዎችን እንደሚያሰማራ ይጠበቃል። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር አባላት በምርጫ ሂደት በሴቶች ላይ በሚደርስ ጥቃት ላይ ትኩረት በማድረግ ሂደቱን በመታዘብ ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን የተለያዩ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን በውስጡ ያቀፈ ሲሆን በምርጫ ሂደቱ ውስጥ አካል ጉዳተኞች የተካተቱ መሆኑን በመታዘብ ላይ ይገኛል። ይህም የመራጮች ምዝገባን እና የምርጫውን ዕለት ያካትታል። በተጨማሪም ኢላማ በተደረጉ አንዳንድ አካባቢዎች በአካል ጉዳተኞች ላይ ያተኮሩ የመራጮች ስልጠና እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከመራጮች ስልጠና ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ለመሥራት እና ምርጫውን ለመታዘብ ያላቸውን ከፍተኛ ፍላጎት የገለጹ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተከታታይ በምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ለውጥ ማድረጉ ዕቅዶቻቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል ብለው እንደሚጠብቁ ገልጸዋል። የዕውቅና አሰጣጥ ሂደቱን ጊዜውን በጠበቀ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ከማከናወን ጋር በተያያዘ መዘግየቶች ስለመኖራቸው ያላቸውን ስጋት የገለጹ አካላት ያሉ ሲሆን ይህም የመራጮች እና የእጩዎች ምዝገባ ሂደቶችን ከነጭራሹ እንዳይታዘቡ አድርጓቸዋል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምህዳሩ ተዘግቶ የቆየ በመሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የፀጥታ ችግሮችን እንዲሁም የአቅም ውስንነቶችን ለመጋፈጥ ተገደዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ከመራጮች ስልጠና እና ከዜጎች ምርጫ መታዘብ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ተግዳሮቶችን የሚፈጥሩ ናቸው። በሀገሪቷ ውስጥ ያለውን ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሁኔታ እና የሲቪል ማህበራት አውድ መስፋቱ አዲስ ክስተት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲቪሉ ማህበረሰብ የሚያሳስቡትን ጉዳዮች ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለማቅረብ የማመንታት ሁኔታ እንደሚታይበት የልዑካን ቡድኑ አስተውሏል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የመራጮች ስልጠና ለመስጠት የገንዘብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን እና ለበርካታ ዓመታት ችግር ያለባቸው ምርጫዎችን ያላለፉ በመሆኑ ተጨማሪ ሀብት እንደሚያስፈልጋቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ይገልጻሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ስልጠና ማቴሪያሎችን በብቸኝነት እያሳተመ መሆኑን የጠቀሱት እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች በተለይም ደግሞ ከአቅሙ ጋር በተያያዘዘ ስጋቶች እንዳሉባቸው ገልጸዋል። ይህም በተገቢው ጊዜ ማቴሪያሎችን አሳትሞ በተለያዩ ቋንቋዎች እና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሁም መደበኛ ትምህርት የማግኘት ውስን ዕድል ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከማሰራጨት አንጻር ችግሮችን አስከትሏል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከአስተዳደራዊ ዕውቅና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ባሉበት ማነቆዎች እና በሀገሪቱ ውስጥ በርካታ አካባቢዎች ላይ ግጭቶች በመጨመራቸው የተነሳ የዕጩዎች ምዝገባ ሂደቱን፣ የቅስቀሳውን ወቅት እንዲሁም የመራጮች ምዝገባን አጀማመር ለመታዘብ ባለመቻላቸው የቅድመ-ምርጫ፣ የምርጫ እና የድህረ-ምርጫ ምህዳሩን በመከታተል ላይ ያተኮሩ ተአማኒነት ያላቸው ከወገንተኝነት ነጻ የሆኑ ድርጅቶች ተስተጓጉለዋል። ይህም ስለ ምርጫው ዑደት ያልተሟላ ስዕል ከመሳል ውጭ ብዙም አማራጭ እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል።

# የመገናኛ ብዙሀን አውድ እና የመረጃ ሁኔታ

በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን አውዱ እና የመረጃ ሁኔታ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ታይቶበታል። የተደረጉት ማሻሻያዎች የፖለቲካ ምህዳሩን ያሰፉ እና ሀሳብን የመግለጽ ነጻትን ያስፋፉ ሲሆን የመገናኛ ብዙሀን አውዱ ከመደበኛ ሚዲያ፣ ከመንግስት እና የግል ጋዜጦች እና የሬዲዮ ጣቢያዎች አልፎ የዲጂታል እና ማህበራዊ ሚዲያዎችን ባካተተ መልኩ እንዲስፋፋ መልካም ዕድልን ፈጥረዋል። ሀገሪቷ በአምባገነን ስርአት እየተገዛች ከመቆየቷ አንጻር እነዚህ ዲጂታል ሚዲያዎች መስፋፋታቸው አዲስ ተሞክሮ ሲሆን ቁጥራቸውም በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል። ሆኖም ግን ሞያው ያላቸው የሚዲያ ድርጅቶች ቁጥር አሁንም አነስተኛ ነው።

ከመገናኛ ብዙሀን አንጻር ያለው ከባቢ ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ድባብ የሚያንጸባርቅ ነው። ዜጎች በብሔር ውጥረት እና በአጠቃላይ ክፍፍል በነገሰበት ከባቢ ሁኔታ፣ በክልሎች እና በጎረቤት ሀገራት መካከል ባለ ግጭት እና በቀጣዩ ምርጫ ሀሳብ ጡዘት ውስጥ ይገኛሉ። መገናኛ ብዙሃን ከመጠን በላይ ፖለቲካ የነገሰባቸው እና በአሁኑ ወቅት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ሰላምንና ደህንነትን ሊጎዳ በሚችል መልኩ የፖለቲካ ወገንተኝነት የማንጸባረቅ አዝማሚያ ይታይባቸዋል። የመንግስት ደጋፊ የሆኑ መገናኛ ብዙሀን የገነኑበት ሁኔታ መኖሩ የተለያዩ መረጃዎችን እና አስተሳሰቦችን ማህበረሰቡ ጋር እንዳይደርሱ የሚገድብ ነው። የደህንነት ስጋቶች መኖራቸው እና የዘር ግጭቶች እየጨመሩ መምጣታቸው ዘገባዎች እንዲገደቡ እንዲሁም የኢንተርኔት እና ሞባይል ኔትዎርክ እንዲዘጋ እና ጋዜጠኞች ዛቻ እንዲደርስባቸው ምክንያት ሆኗል። በርካታ ሰዎች መረጃ የሚያገኙት ከተለመዱት መገናኛ ብዙሀን ሲሆን ይህ በተለይም ደግሞ በገጠር አካባቢ የሚኖረውን እና መረጃ በሬዲዮ የሚያገኘውን ህዝብ በተመለከተ የሚስተዋል ነው። ይህ ዘርፍ ከክልሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው እና ፌዴራል ብሮድካስቲንግ ድርጅቶች ገነው የሚታዩበት ነው።በኢትዮጵያ ኢንተርኔት

የመጠቀም ዕውቀት ያለው ህዝብ ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን እና ከሀገሪቱ ህዝብ ውስጥም የኢንተርኔት መረጃ የሚደርሰው 18.6 በመቶወው ብቻ እሱም አብዛኛው በከተማ አካባቢ የሚኖር ህዝብ እንደሆነ ዓለም አቀፉ የቴሌኮሚኒኬሽን ዩኒየን ያወጣው ሪፖርት ያሳያል። ፌስቡክ ዋነኛው የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ቢሆንም እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያሉ የመንግስት ተቋማትን ጨምሮ አብዛኛው ይዘት በአማርኛ ነው። በቲዊተር ላይ ያሉትን ይዘቶች በተመለከተ በዋነኝነት በእንግሊዘኛ የሚጽፍ እና የዳያስፖራው ማህበረሰብ የሚጠቀምበት ቢሆንም የአማርኛ ይዘቱ መጠን እየጨመረ ይገኛል። ኢትዮጵያ በርካታ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ያሏት ሲሆን በኢንተርኔት ላይ የሚሰስተዋለው የብዝሀነት ማነስ ለበርካታ መራጮች ኢንተርኔትን እንደመረጃ ምንጭ መጠቀምን አዳጋች አድርጎባቸዋል። ለፖለቲካ ፓርቲዎች የብሮድካስት መገናኛ ብዙሀን ላይ በቂ ነጻ የአየር ሠዓት ያልተመደበላቸው መሆኑ እና በጋዜጦች ላይ አቋማቸውን የሚገልጹበት በቂ ቦታ ያለማግኘታቸው የመረጃ ብዝሃነት እንዳይኖር ምክንያት ሆኗል።

የሲቪል እና የምርጫ ተቋማት ያላቸው የአቅም ውስንነት፤ በተለይም በብሔራዊ ደረጃ የምርጫ ቅስቀሳዎችን ማድረግ አለመቻላቸው ችግሩን አባብሶታል። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ሂደቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን በፌስቡክ ይፋ የሚያደርግ ቢሆንም የሚያገኘው ምላሽ እና የሚያጋሩት ሰዎች ቁጥር በመራጮች ምዝገባ ሂደት ላይ እንደሚፈጠሩ መዘግየቶች እና ማራዘሚያዎች ያሉ ለመራጮች ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን በተመለከተም እንኳን ውስን ነው እንዲሁም አካውንቱ ጥቂት ተከታዮች ብቻ ያሉት ነው። በአጠቃላይ በዚህ ግምገማ ሂደት ወቅት የፖለቲካ እና ሲቪል ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይዘቶችን ለማጉላት ያደረጉት ጥረት የለም። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚለጠፉ የፌስቡክ ይዘቶች በአማርኛ ብቻ ቢሆኑም በኢንተርኔት የሚለቀቁ የመራጮች ስልጠና ማቴሪያሎች በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በአፋን ኦሮሞ፣ በአፋርኛ፣ በሶማሊኛ እና በትግርኛ ተሰራጭተዋል።

በኢትዮጵያ የኢንተርኔት መረጃ እና የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም መጠን መጨመሩ በቂ የመራጮች ስልጠና ሥራ ካለመሰራቱ፣ የብሄር እና የቋንቋ ውጥረቶች ከመካረራቸው እና ለምርጫው ከሚሰጠው ትልቅ ቦታ ጋር ተደምሮ ሀሰተኛ መረጃዎች የሚሰራጩበትን ዕድል ሊያሰፋው ይችላል። በርካታ የፖለቲካ ተዋንያን የሀሰት መረጃን ከማሰራጨታቸው ጋር ተያይዞ የሀሰተኛ መረጃ እና የጥላቻ ንግግሮች ስርጭት በመጨመር ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህም ችግሩን የሚያባብስ እና ህዝብን የሚያሳስት ነው። ምንም እንኳን ፖለቲከኞች ትክክለኛ አካውንታቸውን ተጠቅመው የሀሰት እና የጥላቻ ይዘቶችን ባያሰራጩም ይፋዊ ያልሆኑ ገጾች፣ የደጋፊዎቻቸው ቡድኖች፣ ወገንተኛ መገናኛ ብዙሀን እና ኢንተርኔት ላይ የሚንቀሳቀሱ አክቲቪስቶች በምርጫው ዙሪያ ባለው የፖለቲካ ውይይት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጠብ አጫሪ ወይም አሳሳች ትርክቶችን በማመንጨት ወይም በማጉላት ላይ ያሉ ሲሆን ይህም ይህም የብሔር ውጥረቶችን ሊያባብስ እና በምርጫው ሂደት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ስጋት ከፍ ሊያደርግ ይችላል። የኢንተርኔት ተደራሽነት ዝቅተኛ ቢሆንም በገጠር አካባቢዎችም ጭምር ሀሰተኛ መረጃዎች ሊሰራጩ ይችላሉ፤ ለዚህም ምክንያቱ የሚደርሳቸውን መረጃ ትክክለኛነት የሚያጣሩባቸው ውጤታማ መንገዶች ላይኖሯቸው ስለሚችል ነው።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የማህበራዊ ሚዲያ አውዱ ላይ ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አንዳንድ አግባብ ያልሆኑ የማህበራዊ ሚዲያ ተግባራትን ያወገዘ ቢሆንም ያንን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመከታተል እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አቅም ያንሰዋል።

# ምስጋና

ኤንዲአይ እና አይአርአይ የዚህን የልዑካን ቡድን ሥራ እና ሌሎች በመከናወን ላይ ያሉ የምርጫ ግምገማ ሥራዎችን በመደገፉ ለዩኤስኤአይዲ ምስጋናቸውን ይገልጻሉ። ሪፖርቱ የኤንዲአይ እና አይአርአይ ከአድሎ ነጻ የሆነ እና ገለልተኛ ትንታኔ የቀረበበት ነው። አይአርአይ እና ኤንዲአይ በመላው አለም የዴሞክራሲ ተቋማትን ለመደገፍ እና ለማጠናከር እንዲሁም ነጻነትን ለማስፋፋት የሚሰሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ እና ከፓርቲ ውግንና ነጻ የሆኑ ድርጅቶች ናቸው። ኤንዲአይ እና አይአርአይ በድምሩ ከ400 በላይ ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢነት ተልዕኮዎችን እንዲሁም ከ65 በላይ በሆኑ ሀራት ውስጥ ግምገማዎችን አከናውነዋል። በኢትዮጵያ የምርጫ ከባቢ ሁኔታ ላይ ተቋማቱ የሚያደርጉት ቀጣይነት ያለው ግምገማ የሚከናወነው በአለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢነት መርሆዎች ዲክላሬሽን እና በኢትዮጵያን ሕጎች መሰረት ነው።

ስለ አይአርአይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- www.iri.org

ስለ ኤንዲአይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- www.ndi.org

የ2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫን በተመለከተ የአይአርአይ-ኤንዲአይ (IRI-NDI) የምርጫ ታዛቢ ልዑካን ቡድን የቅድመ ምርጫ ግምገማ ሪፖርት


ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት

1225 Eye Street NW, Suite 800
Washington, DC 20005

info@iri.org

ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት

455 Massachusetts Ave NW, 8th
Floor Washington, DC 20001

http://www.ndi.org/contact